*ምዕራፍ ።*

# መካንነት እና ቤተ ክርስቲያን መትከል

መካንነት ሲወገድ፣ ውጤቱ ፍሬያማነት ይሆናል። በዚህ ዘመን ባለች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላለው የቤተ ክርስቲያን መትከል ጉድለት ዋነኛው ምክንያት መካንነት ነው። እግዚአብሔር ግን ፍሬያማዎች እንድንሆን ይፈልጋል። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያናትን እንድንተክል ይፈልጋል። ፍሬያማ እንድትሆን መካንነት በእርግጥ ምን እንደሆነ ልትረዳ ይገባል። አንዳንድ መጋቢዎች መካን ናቸው። ምንም ነገር ቢያደርጉ፣ አገልግሎታቸው በፍጹም አያብብም። እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ እንድንመረምር የሚፈልገው ችግር ይህ ነው።

በሚቀጥሉት ጥቂት ምዕራፎች ውስጥ፣ መንፈሳዊ መካንነት የሚለውን ሐሳብ እና በቤተ ክርስቲያን መትከል ላይ የሚያመጣውን ተፅዕኖ እናጠናለን። በእኛ ትውልድ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ተከላ አለመኖር ዋነኛ ምክንያት መካንነት ነው። ብዙ እንቅስቃሴዎችና ብዙ ፕሮግራሞች አሉ ግን በጣም ጥቂት ወይም ምንም ዓይነት ቤተ ክርስቲያን የመትከል ሥራ የለም።

በሕይወታችን፣ በቤተ ክርስቲያን እና በአገልግሎቶች ውስጥ ያለውን መካንነት ምክንያት ስናጠና እግዚአብሔር ይገልጥልናል።



'መካንነት' ወደሚለው ቃል የተተረጎሙ የተለያዩ የዕብራይስጥ እና የግሪክ ቃላቶች አሉ። እነኚህ ቃላቶች በመንፈሳዊ እና በአገልግሎት መካንነት ጉዳይ ላይ ብርሃንን ይፈነጥቃሉ። እነኚህን እያንዳንዳቸውን ቃላቶች ለመካንነት ፍች እንደተሰጡ እንመልከት።

## አምስት የዕብራይስጥ ቃላቶች

### 1. አቁ(AQAR) — (ዘፍጥረት 11:30፣ መሳፍንት 13:2,3፣ ዘፍጥረት 25:21፣ 1ኛ ሳሙኤል 2:5፣ ዘዳግም 7:14)

ይህ ቃል፣ "ዘር አመንጭ የሆነው ብልት መውደም ወይም መወገድ" ማለት ነው። በተጨማሪም፣ 'የማይሠራ ብልት መኖር፣ መካን ወይም ጭንጫ'፣ ማለት ነው።

ይህ ቃል እንደ ሣራ፣ ዘልፎኒ፣ የሳምሶን እናት እና ርብቃን የመሳሰሉ ሰዎችን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል።

> **በምድርህም ፅንስ የሚያስወርዳት ወይም መካን(አቂ) ሴት አትኖርም፤ ረጅም ዕድሜም እሰጥሃለሁ።**
>
> **ዘፀአት 23:26**
> **(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)**

ከ'አቁ (AQAR)' መካንነት የተነሣ በመሠቃየት ላይ ያሉ ቤተ ክርስቲያናት ወይም ግለሰቦች፣ አመንጪ የሆነው የአገልግሎት ሁኔታ እጥረት ያለባቸው ናቸው። ይህ ማለት የወንጌል ስርጭት እና ፍሬ የሚያፈራ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት እጥረት አለባቸው ማለት ነው። ሌሎች ቤተ ክርስቲያናትን መውለድ የማይችሉ ናቸው። እንደዚህ ያሉት ቤተ ክርስቲያናት ብዙ እንቅስቃሴዎች አሏቸው፣ ግን ሌሎች ቤተ ክርስቲያናትን የሚያፈልቁ ፕሮግራሞች የሉም።

ሁሉም አገልጋይ የአገልግሎቱን የወንጌል ስርጭት ሁኔታ ስፍራ ሊሰጠው ይገባል። ክሩሴዶችን ታካሂዳለህ? አዲስ ቤተ ክርስቲያናትን ትተክላለህ?

የክሩሴዶች፣ የቁርስ ስብሰባ፣ የምስክርነት ዘመቻዎች እና ቤተ ክርስቲያን መትከል፣ አለመኖር የአገልግሎትህን የአመንጪነት እጥረት ያሳያል።

መካን ሰዎችም ቃሉን ሊቀበሉና ምናልባም የስብከት ካሴቶች ሊኖራቸው ይችላል። ምናልባትም በሌሎች የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴዎች ተሳታፊ ሊሆኑ ይችላሉ። በጸሎት ፕሮግራሞች ላይ ሊታዩና በመንፈስ "የደለቡ" ሊሆኑ ይችላሉ።

ቢሆንም ግን፣ እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን በመትከል፣ በወንጌል ስብከት ወይም ነፍሳትን መማረክ ላይ ተሳታፊ አይሆኑም። አመንጪ በሆነው መንፈሳዊ ብልታቸው(አካል) ላይ እጥረት አለባቸው።

## 2. ሻኮል(SHAKOL) - (ዘሌዋዊያን 26:22፣ 2ኛ ነገሥት 2:19፣ ዘዳግም 32:25)

ይህ ማለት 'መጨንገፍ፣ ውርጃ፣ የልጆች ሞት፣ መካንነት፣ ጽንስ ማስወረድ፣ ልጅ አልባ መሆንና ለልጅ አለመታደል' ማለት ነው።

> የዱር አራዊትን እሰድባችኋለሁ፣ ልጆቻችሁን ይነጥቋችኋል፣ ከብቶቻችሁን ያጠፉባችኋል፣ ቁጥራችሁ ይመነምናል፣ መንገዶቻችሁም ሰው አልባ (ሻኮል) ይሆናሉ።
>
> ዘሌዋውያን 26:22
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

እንደነኚህ ዓይነቶቹ ቤተ ክርስቲያናት ወይም አገልጋዮች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ነፍሳት መያዝ አይችሉም፣ ማየት እንደምትችለው፣



በማያቋርጥ ሁኔታ በፅንስ ውርጃ እና ፅንስ መቋረጥ ይጠቃሉ። እንደነኚህ ዓይነት አገልጋዮች ቀጣይነት ያለው እድገት የሌላቸው እና እግዚአብሔር በሰጣቸው ነገር ላይ መግፋት የማይችሉ ናቸው።

ብዙ ቤተ ክርስቲያናት ብዙ እንግዶችንና(ጎብኚዎችን) አዲስ የተለወጡ ነፍሳትን ያገኛሉ። እነኚህ አዲስ የተለወጡ ነፍሳት የመጠበቅ ሥራ ልትሠራ ይገባል። ጎብኚዎችህ እንደገና ተመልሰው እንደሚመጡ ማረጋገጥ አለብህ እኔ ሁል ጊዜ በአባላቶቼ ላይ እጸልያለሁ።

"ጌታ ሆይ ከሄዱ በኋላ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን ተመልሰው ይምጡ። ሲመለሱ ደግሞ፣ ብዙ ሰዎችን ይዘው ይምጡ። "እንዲህ ዓይነቱ ጸሎት "ሻኮል" መካንነትን መልሶ ያጠቃል። እያንዳንዱ አባል አገልጋይ እንዲሆን እና እያንዳንዱ አገልጋይ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን እንዲወልድ እጸልያለሁ።

ሌላው እንደነኚህ ያሉ ቤተ ክርስቲያናት መውጣት የማይችሉበት ምክንያት ወጣት መሪዎቻቸውን ስለሚያጠቁ ነው። ትኩስ ኃይሉን ይገድላሉ። መሪዎች በዙሪያቸው እንዲያብቡ አይፈልጉም። በአገልግሎትህ ውስጥ አዲስ መሪዎችና መጋቢዎችን ለመልቀቅ መፍቀድ አለብህ። ሁልጊዜ ፈጣን እድገት የሚገኘው ብዙ አገልጋዮች በአንድነት ሲሠሩ ነው።

## 3. ሚልቻሕ MELECHAH (2ኛ ነገሥት 2:19፣ መዝሙር 107:34፣ኤርሚያስ 17:6)

ይህ ቃል "የጨው ምድር" ፣ "በረሃ ወይም መካን ምድር" ማለት ነው። የሚናገረው ስለ "ምርት አልባነት" እና "ሕይወት አልባነት" ነው። ለማንኛውም ዓይነት ዘር የማይሆን ሙት የሆነ ምድር ማለት ነው።

በ"ሚልቻኽ" እየተሰቃዩ ያሉ ሰዎች በመንፈስ የጨው ምድር ናቸው። የፈለገውን ነገር ብታፈስባቸው፣ ፍሬ ማፍራት አይችሉም። ዘር ማብቀል የማይችሉ ናቸው።

እያንዳንዱን ጉባዔ ለአፍታ ብትመለከት ብዙ "የጨው ምድሮች" ሲመለከቱህ ታያለህ። ምሕረት እና ይቅርታ! ለብዙ ዓመታት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩና ብዙ ስብከቶችን የሰሙ ናቸው። በተለየ ሁኔታ ተቀብተው የተጸለየላቸው ናቸው፣ ግን ይሁንና አሁንም ፍሬ ሊያፈሩ አልቻሉም። እነኚህ ጨዋማ የሆኑት ብዙ ፈሰባቸዋል ግን የሚጠበቅባቸው ጥቂት ሊሆን ይችላል።

ጨዋማ የሆኑ ቤተ ክርስቲያናትም አሉ። የፈለገውን ያህል ጥረት ቢደረግ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ አታድግም። ከዚያች ቤተ ክርስቲያን ምንም አዲስ ቤተ ክርስቲያን አይተከልም። ጨዋማ ምድሩ እስኪፈወስ ድረስ፣ ፍሬ አይኖርም።

> የከተማይቱም ሰዎች ኤልሳዕን፣ "እነሆ ጌታችን፣ እንደምታያት ይህች ከተማ ለኑሮ የተመቸች ናት፤ ይሁን እንጂ ውሃው መጥፎ ሲሆን ምድሪቱም ፍሬ የማትሰጥ(ሚልቻኽ) ናት" አሉት። እርሱም፣ "እስቲ በአዲስ ማሰሮ ጨው ጨምራችሁ አምጡልኝ" አለ፤ እንዳለውም አመጡለት። ከዚያም ወደ ውሀው ምንጭ ሄዶ ጨው ጣለበትና "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ 'ይህን ውሃ ፈውሼዋለሁ፤ ከእንግዲህ ወዲያ ለሞት ምክንያት አይሆንም ምድሪቱንም ፍሬ እንዳትሰጥ አያደርጋትም' አለ።" ኤልሳዕ እንደ ተናገረውም ውሃው እስከ ዛሬ ድረስ የተፈወሰ ነው።
>
> 2ኛ ነገሥት 2፡1 9-22
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

የጨው ምድር የሆነ መጋቢ እንደርሱ ያሉ ሌሎች መጋቢዎችን አያስነሣም። በሚመግብበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይቆያል፣ ግን ሌሎች



መጋቢዎችን አያፈራም። ከጨውነት ጥስህ በመውጣት ሌሎች ብዙ ቤተ ክርስቲያናትን ስለ መውለድ አስብ።

ስለ አንድ ልታድግ ስላልቻለች ቤተ ክርስቲያን አስታውሳለሁ። ምንም ይሁን ምን ወይም ቢሰብክ፣ መጣስ የሚባል ነገር አልነበረም። አንድ ቀን አንድ ተጋባዥ መጋቢ ጌታን ሲጠብቅ ራእይ ተመለከተ። በኮርኒሱ ላይ ከፍ ብሎ አንድ አጋንንት በጉባዔው ላይ ተቀምጦ አየ። ይህ ክፉ መንፈስ ለብዙ ዓመታት ቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ተጽዕኖ አድረጎ ነበር። እግዚአብሔር የመጋቢውን ዓይን ከፍቶ ቤተ ክርስቲያኑ መካን እንዲሆን ያደረገውን "ጨው" እንዲመለከት አደረገ። ያንን ክፉ መንፈስ ተቋቁሞ እንዲለቅ አዘዘው። ከዚያ በኋላ ቤተ ክርስቲያኒቱ በከፍተኛ ፍጥነት ማደግ ጀመረች።

የእግዚአብሔር የፈውስ እጆች የሚያስፈልጓቸው የእውነት ጨዋማ ሁኔታዎች እንዳሉ አምናለሁ። እግዚአብሔር ጨዋማነትን ከሕይወትህ፣ ከቤተ ክርስቲያንህ እና ከአገልግሎትህ ላይ ሲያነሣ ይታየኛል!

## 4. ኦትሰር OTSER — (ምሳሌ 30:16)

ይህ የዕብራይስጥ ቃል፣ "መዝጋት"፣ ወደ ኋላ ይዞ ማስቀረት፣ መያዝ፣ ማለት ነው። እንደገናም መዝጋት፣ መቆጣጠር፣ መያዝ፣ ማለት ነው። በተጨማሪም፣ መዝጋት፣ መግታት እና ማቆም ማለት ነው።

> እነርሱም መቃብር፣ መካን(ኦትሰር) ማኅፀን፣ ውሃ ጠትታ የማትረካ ምድር፣ "በቃኝ" የማይል እሳት ናቸው።
>
> ምሳሌ 30፡16
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ሰዎች እንደዚህ ባለ ሆን ብሎ ወደ ኋላ በሚያስቀር መካንነት እየተሠቃዩ ነው። ብዙ ያውቃሉ፣ ግን ወደኋላ በማለት ፍሬ ለማፍራት እንቢ ይላሉ። "ኦትሰር" መካንነት ያለባቸው መጋቢዎች ቤተ ክርስቲያን

ለመትከል የገንዘብ አቅሙና ቅባቱ አላቸው። ይሁን እንጂ፣ ይህን አቅማቸውን እንደ፦ የሙታን ልጆች ማሳደጊያ፣ ትምህርት ቤት እና ማኅበራዊ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ያውሉታል፤ አንዳንዶቹ ፖለቲካዊ ተጽዕኖ ማምጣት እና በማኅበረሰቡ ተቀባይነት ማግኘት ላይ ይበልጥ ያተኩራሉ። ቤተ ክርስቲያን የመትከል ተነሣሽነታቸው የተገደበ ነው።

እንደነኚህ ዓይነት ሰዎች ለጌታ ብዙ ነገሮችን ማድረግ ይችላሉ፤ ግን ይህን ከማድረግ የተቆጠቡ እና ችሎታቸውን ወደኋላ የሚይዙ ናቸው። እነኚህ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ በጌታ ብዙ ልምምድ ያላቸውና ለኢየሱስ አብዝተው መሥራት የሚችሉ ናቸው።

አብዛኛውን ጊዜ አቅምና ጊዜያቸውን ለሌሎች ለማዋል የወሰኑ ናቸው። በጉባዔህ ውስጥ፣ የአብሮ አደጎች ማኅበር ወይም የፖለቲካ ቡድኖች መሪ የሆኑ ሰዎችን ታያለህ። ለፖለቲካ፣ እግር ኳስ፣ ለማስትሬት ዲግሪ እና ለዶክትሬት ዲግሪ እና ለሌሎች እንቅስቃሴዎች ጊዜ አላቸው። ሆኖም ግን፣ ወደ እግዚአብሔር ሥራ ሲመጣ፣ የተዘጉ እና የተገደቡ ናቸው። የጸሎትና የአምልኮ ጉዳይ ሲሆን ቁጥቦች ናቸው፣ ግን ለፖለቲካና ለሌሎች ጉዳዮች አፋቸው ይከፈታል። እነኚህ ሰዎች ናቸው፣ በ'ኦትሰር' እየተሠቃዩ ያሉ።

## 5. ጺያህ 'TSIYAH' — (ኢሳይያስ 41፡18፣ መዝሙር 63፡1)

ይህ ቃል የሚገልጸው 'ንቃቃን እና መካን' መሆንን ነው። ስለ 'ዱር፣ ደረቅ ምድር እና ምድረ በዳነት' ይናገራል።

> በተራቆቱ ኮረብቶች ላይ ወንዞችን፣ በሸለቆዎች ውስጥ ምንጮች አፈልቃለሁ። ምድረ በዳውን የውሃ ኩሬ፣ **የተጠማውን ምድር(ጺያህ)** የውሃ ምንጭ አደርጋለሁ።
>
> ኢሳይያስ 41፡18
>
> (በአዲሱ መደበኛ ትርጉም)



እንደዚህ ዓይነቱ ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ድርቀት ያለበት ነው። አምልኮ፣ ጸሎት እጆችን ወደ ላይ መዘርጋት የሌለበት ምድረ በዳ ነው። እንደዚህ ያሉ ቤተ ክርስቲያናት ሰዎች ለሕይወት እና ለአገልግሎት ያላቸው አመለካከት ሥጋዊ እና በአዕምሮ ስሌት መንፈሳዊ ነገርን ለመርዳት የሚሞክሩ ናቸው። መንፈሳዊ ድርቀት እና አለ ማምለክ የመካንነት እውነተኛ ምክንያቶች ናቸው።

አዳዲስ የአምልኮ ዝማሬዎችን ማስተዋወቅ አብዛኛውን ጊዜ እንዲህ ዓይነቱን መካንነት ይዋጋል። አንዳንድ ጊዜ የአምልኮ መሪህን መለወጥ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ከፍተኛ ለውጥ ይመጣል። የመዘምራን መሪን እና የመዘምራን ቡድኑ የሚዘምሯቸውን መዝሙሮች መለወጥ ቤተ ክርስቲያንህ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ይችላል። ምናልባት መዘምራኑ ነፍሳትን ስለ መማረክ እና የጠፉትን ስለ መድረስ ቢዘምሩ፣ ቤተ ክርስቲያን ተከላ ሊጀምር ይችላል። ለውጥ ማምጣት የሚገባህን ነገሮች ከመለወጥ ወደ ኋላ አትበል።

## ሁለት የግሪክ ቃላቶች

### 1. ስቲራስ 'STEIRAS' — (ሉቃስ 1፡7,36፣ ሉቃስ 23፡29፣ ገላቲያ 4፡27)

> ይሁን እንጂ ኤልሳቤጥ መካን(ስቲራስ) በመሆኗ ልጅ አልነበራቸውም፤ ሁለቱም በዕድሜ የገፉ ነበሩ። እነሆ፣ ዘመድሽ ኤልሳቤጥም በእርጅናዋ ልጅ ፀንሳለች፤ መካን የተባለችውም ስድስተኛ ወሯን ይዛለች፤
>
> ሉቃስ 1፡7፣ 36
>
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ይህ ቃል፣ "ደረቅ(ጠንካራ) መሆን እና በተፈጥሮ ያልተለመደ" ማለት ነው። ጭንጫ እና መካን ስለመሆን ያስረዳል። "ደረቅነት" የሚያስረዳው ለእግዚአብሔር ቃል ስለማይበገሩ እና ስለማይታዘዙ ሰዎች ነው። ለእግዚአብሔር ቃል የማይታዘዝ ማንኛውም ሰው መካን ይሆናል።

እንደነኚህ ያሉ ሰዎች የታወቁና የላቁ ሆነው መታየት ይፈልጋሉ። አንዳንድ ጊዜ መንፈሳዊ ሰው መስለው መታየት ይፈልጋሉ ግን አይደሉም።

ቤተ ክርስቲያናት አብዛኛውን ጊዜ እንደነኚህ ላሉ መንፈሳዊ ላልሆኑ እና ደረቅ ሰዎች የፊት ወንበራቸውን ይሰጣሉ። ይህን ማድረግ እድገትን በመግታት እድገት የሚከለክለውን 'ክቲፊስ' ሁኔታን ይጋብዛል። በሚያድጉ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ሕያው፣ በጋለ ስሜት የተሞሉ፣ መደነቅ የሞላባቸው ሰዎች ሲደንሱና ጌታን ሲያወድሱ ታያለህ። 'በጣም የቀዘቀዙትን' ከዋነኛው ቦታ የማስወገድ ጊዜው አሁን ነው። ቤተ ክርስቲያን 'የማንነት' መታያ ስፍራ አይደለችም።

## 2. አርጎስ 'ARGOS' (2ኛ ጴጥሮስ 1:8)

ይህ ቃል፣ "የማይንቀሳቀስ፣ *ሥራ ፈት* ሰነፍ እና ዋጋቢስ" ማለት ነው። በተጨማሪም "ከንቱ መሆን፣ ዝግተኛ እና መካን"፣ ማለት ነው። የሚደንቀው፣ ስንፍና በአገልግሎት ውስጥ የፍሬ አልባነት ዋነኛ ከሆኑት ምክንያቶች ውስጥ አንደኛው ነው። ሰነፍ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንቅስቃሴ አያደርጉም። ስንፍናቸው ለእግዚአብሔር የማይጠቅሙ ያደርጋቸዋል።

> እነዚህ ነገሮች ለእናንተ ሆነው ቢበዙ፣ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት *ሥራ ፈቶች*ና፣ ፍሬ ቢሶች(አርጎስ) እንዳትሆኑ ያደርጉአችኋልና።
>
> 2ኛ ጴጥሮስ 1:8

የሚያሳዝነው ግን፣ ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ደካማ በሆኑ ብዙዎች የተሞላች መሆኗ ነው። ይህን ዓይነቱን መካንነት ለመስበር፣ ስለ ትጋት መስበክ በጣም አስፈላጊ ነው። ጉባዔህ ነፍሳትን ለጌታ መማረክ እንዳለበት ማስተማር በጣም አስፈላጊ ነው።

*ከዚህም ሁሉ በላይ፣ ልጄ ሆይ፣ ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም፤*



*ምዕራፍ 12*

# መካንነትን እንዴት ለይቶ ማወቅ እንደሚቻል

በአገልግሎት ውስጥ መካንነት በሚኖርበት ጊዜ ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል። ችግሩን ማወቅ ብዙውን ጊዜ ወደ መፍትሔ ያመራል። በሕክምና እንኳ፣ ምርመራ ከተካሄደ 80% የሚሆነው ችግራችን ይቃለላል።

ብዙ አገልግሎቶች በመካንነት መንፈስ ውስጥ እየሠሩ ነው። ብዙ መጋቢዎች የበለጠ የፍሬያማነት ደረጃ ሊኖራቸው እንደሚችል አያውቁም። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ፣ በአገልግሎትህ ውስጥ ለይተህ ልታውቃቸው የሚገቡህን ምልክቶች አሳይሃለሁ።

ኢየሱስ በአጠገብህ ቢቆም፣ እንዲህ ይልህ ነበር።

> ብዙ ፍሬ በማፍራት ደቀ መዛሙርቴ መሆናችሁን ብትገልጡ፣ በዚህ አባቴ ይከብራል።
>
> የሐንስ 15:8
>
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

## በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት መካንነትን ለይቶ ማወቅ ይቻላል

መካንነትን የመለየት አንዱ መንገድ መዝገበ ቃላት መካንነትን እንዴት እንደሚፈታው መመልከት ነው። እነኚህን ፍችዎች ቤተ ክርስቲያንህ ላይ ብትጠቀምባቸው፣ መካን መሆንህንና አለመሆንህን ታውቃለህ። የመካንነት መንፈስ በመሥራት ላይ ከሆነ እግዚአብሔር ያሳይሃል።

አሁን በመዝገበ ቃላት ላይ የሚገኙ የመካንነት ፍችዎችን በመመልከት እንዴት በአገልግሎት ላይ እንደሚሠሩ እንመልከት።

## የመካንነት ሃያ ፍችዎች

1. መካንነት ፍሬ አልባ መሆን ማለት ነው
2. መካንነት ጭንጫ መሆን ማለት ነው
3. መካንነት ልጅ አልባ፣ ወራሽ የሌለው እና ተተኪ የሌለው ማለት ነው
4. መካንነት ማለት ምርታማ ያልሆነ ማለት ነው
5. መካንነት የምርታማነት እጥረት ያለበት ማለት ነው
6. መካንነት ማለት በፍጹም አትጸንሥም ወይም አታመነጭም ማለት ነው
7. መካን የሆነ ሰው በጣም ጥቂት የሆነ ምርት ያመርታል
8. መካን ምድር ጠፍ መሬት ነው
9. መካን ዛፎች ትክክለኛውን ፍሬ አያፈሩም
10. መካንነት ገላጣነትን ያሳል
11. መካን መሆን መሟጠጥ ነው
12. መካን መሆን ምድረ በዳ መሆን ነው
13. መካንነት ደረቅነትን ያሳያል
14. መካን የሆነ ማለት፣ የማይበራከት ነገርን ያሳያል
15. መካን ምድር፣ ትንሽ ምድር ነው
16. መካንነት አንዳንድ ጊዜ ደነዝነትን ያሳያል
17. መካን የሆነ ሰው መሰሉን አያፈራም
18. መካንነት የመጸነሥ ኃይልን መፈለግ ወይም ማስፈለግ ያሳያል
19. መካን ስፍራዎች የደኸዩ ናቸው
20. መካን ቦታዎች ሊታረሱ አይችሉም



አሁን ደግሞ ከቤተ ክርስቲያን አኳያ የመካንነት ምልክቶችን እንመልከት። አገልግሎትህን በመመርመር መካንነት መኖሩን ተመልከት

## መካንነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ

ከሚከተሉት ውስጥ ማንኛውም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካለ መካንነት አለ ማለት ይቻላል፦

1. የቤተ ክርስቲያን አባላቶችህ ብዛት የማይጨምር ከሆነ
2. አዲስ የተለወጡ ሰዎች ከሌሉ፣ ወይም አዲስ የሚለወጡ ሰዎች ብዛት የማይጨምር ከሆነ
3. ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ሰዎች ቁጥር የማይጨምር ከሆነ
4. የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ቁጥር የማይጨምር ከሆነ
5. የውሃ ጥምቀት ከሌለ ወይም፣ የሚጠመቁ ሰዎች ብዛት የማይጨምር ከሆነ
6. ፈውስና ተአምራት ከሌሉ
7. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ መሪዎች ብዛት የማይጨምር ከሆነ
8. እግዚአብሔርን ማወቅ የማይጨምር ከሆነ
9. የግንኙነት ሥር መስደድ የማይኖር ከሆነ
10. በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጡ ራእዮች እና ሕልሞች ብዛት የማይጨምር ወይም ከቶውንም የሌለ ከሆነ
11. የወንጌል መልእክተኞችን የመላክ መርሃ ግብር ከሌለ ወይም፣ የሚላኩ የወንጌል መልእክተኞች ቁጥር የማይጨምር ከሆነ
12. የቤተ ክርስቲያን የገንዘብ አቅም የማይጨምር ከሆነ
13. የምታውቃቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ብዛት የማይጨምር ከሆነ
14. የአገልግሎት ልምድህ የማይጨምር ከሆነ

15. የቤተ ክርስቲያን የወንጌል ስርጭት መውጣት ከሌለ ወይም፣ እድገት ከሌለው።
16. የጸሎትህ ስፋትና ጥልቀት እድገት ከሌለውና ወይም ጸሎት ከሌለ
17. ተግዳሮቶችና የምታሸንፋቸው ተራሮች ካልጨመሩ
18. ለላቀ ራእይ ተግዳሮትና መነሣሣት ከሌለ
19. የመረዳት ዕድገት ከሌለ
20. የኅብረቶችና ቅርንጫፍ(አጥቢያዎች) ዕድገት ከሌለ

አሁን ችግሮችን መርምረሃል፣ ለአገልግሎትህ የጌታን ትንቢት ተቀበል። እነኚህ ቃሎች በሕይወትህ እንደሚፈጸሙ እመን።

**አንቺ ያልወለድሽ መካን ሆይ፣ ዘምሪ አንቺ ያላማጥሽ ሆይ፣ እልል በይ ጩኺም ባል ካላት ይልቅ ፈት የሆነቺቱ ልጆች በዝተዋልና፣ ይላል እግዚአብሔር። የድንኳንሽን ስፍራ አስፊ፣ መጋረጃዎችሽንም ይዘርጉ፣ አትቆጥቢ አውታሮችሽን አስረዝሚ ካስሞችሽንም አጽኚ። በቀኝና በግራ ትሰፊያለሽና፣ ዘርሽም አሕዛብን ይወርሳልና የፈረሱትንም ከተሞች መኖሪያ ያደርጋልና። አትፍሪምና አትፍሪ አትዋረጂምና አትደንግጪ የሕፃንነትሽንም እፍረት ትረሺዋለሽ፣ የመበለትነትሽንም ስድብ ከእንግዲህ ወዲህ አታስቢም። ፈጣሪሽ ባልሽ ነው፣ ስሙም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው የእስራኤልም ቅዱስ ታዳጊሽ ነው፣ እርሱም የምድር ሁሉ አምላክ ይባላል። እግዚአብሔር እንደተተወችና እንደ ተበሳጨች በልጅነትዋም እንደ ተጣለች ሚስት ጠርቶሻል፣ ይላል አምላክሽ። ጥቂት ጊዜ ተውሁሽ፣ በታላቅም ምሕረት እሰበስብሻለሁ። በጥቂት ቁጣ ለቅጽበት ዓይን ፊቴን ከአንቺ ሰወርሁ፣ በዘላለምም ቸርነት እምርሻለሁ ይላል ታዳጊሽ እግዚአብሔር።**

ኢሳይያስ 54፡1-8

*ከዚህም ሁሉ በላይ፣ ልጅ ሆይ፣ ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም!*



*ምዕራፍ 13*

# የተለያዩ ዓይነት መካንነቶችን እንዴት መዋጋት ይቻላል

## የሽምግልና ዕድሜ መካንነትን መዋጋት

አብራም ሦራን አገባ፣ ሦራ ግን ልጅ ልትወልድ አልቻለችም

ዘፍጥረት 11፡30

(Contemporary English Verion)

የአብራም ሚስት ሦራ ግን ለአብራም ልጅ አልወለደችም ነበር ስምዋ አጋር የተባለ ግብፃዊት ባሪያም ነበረቻት። ሦራም አብራምን፦ እነሆ እንዳልወልድ እግዚአብሔር ዘጋኝ፣ ምናልባትም ከእርስዋ በልጅ እታነጽ እንደሆነ ወደ እርስዋ ግባ አለችው። አብራምም የሦራን ቃል ሰማ። አብራምም በከነዓን ምድር አሥር ዓመት ከተቀመጠ በኋላ፣ የአብራም ሚስት ሦራ ግብፃዊት ባሪያዋን አጋርን ወስዳ ለባልዋ ለአብራም ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠችው። እርሱም ወደ አጋር ገባ፣ አረገዘችም እንዳረገዘችም ባየች ጊዜ እመቤትዋን በዓይንዋ አቃለለች።

ዘፍጥረት 16፡1-4

ሁላችንም የአብርሃምን እና የሣራን ታሪክ እናውቃለን። ሣራን እንደ አንዲት ቤተ ክርስቲያን አድርገህ ልትመለከት ትችላለህ። እንደ አንድ አገልግሎትም አድርገህ ልትመለከት ትችላለህ። ሣራ የሚገባውን ያህል ፍሬ እንዳላፈራ እንድ መጋቢ ልትታይ ትችላለች። ሣራ ሕይወት በሌለበት በረሃማ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ልትመስል ትችላለች።

## 1. የወንጌል ስርጭት እና ቤተ ክርስቲያን የመትከል ኃላፊነት ለማንም አሳልፈህ አትስጥ

መጋቢው ጉባዔውን ነፍሳትን ወደ መማረክ እና ፍሬ ወደ ማፍራት መምራት አለበት። እንደ ዘፍጥረት 16፡2፣ ሣራ ልጅ የማፍራት ኃላፊነትን ለሌላ ሰው አሳልፋ ሰጠች። ይህ የነበረባትን መካንነት የማሸነፍ ሙከራ ነበር። መካንነትን ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ለማሸነፍ ሞከረች።

## 2. ትንቢታዊ ቃልን አትጣል

ሣራም በልብዋ እንዲህ ስትል ሳቀች፡- ካረጀሁ በኋላ በውኑ ፍትወት ይሆንልኛልን? ጌታዬም ፈጽሞ ሸምግሎአል።

ዘፍጥረት 18፡12

ትንቢታዊ መልእክት በአገልግሎትህ ላይ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል። በእግዚአብሔር እመን ትጸናማለህ፣ በነቢያቱም እመን ይሳካልህማል። ሣራ ስለ ይስሐቅ የተነገረውን ትንቢት ስትሰማ ሳቀች። በመገለጥ፣ በሕልም፣ እና በሚነገሩ ቃላት፣ በሕይወትህ ላይ የሚመጣውን የእግዚአብሔር ጉብኝት ተቀበል።

ከዓመታት በፊት፣ ከአንድ ነቢይ መልእክት ተቀበልሁ። የሚበራ የእጅ ባትሪ ይዤ ብዙ ሕዝብ ስመራ ተመለከተ። ይህንን መልእክት የሰጠኝ እ.ኤ.አ 1980 ውስጥ ነበር። ሃያ አራት ዓመታት አለፉ፣ ግን ይህ ትንቢት እውነተኛ ራእይ እንደሆነ በልቤ ውስጥ አለ። ተማሪ ሆኜ የእግዚአብሔርን ሥራ እንድሠራ አበረታታኝ። ከትምህርት ቤት በኋላም በአገልግሎት እንድጸና አበረታታኝ።



## 3. በእግዚአብሔር፣ በነቢያቶቹ እና በቃሉ ስብከት እመን

እግዚአብሔር አብርሃምን እንዲህ አለው፤ ሦራን ከእንግዲህ ሦራ ብለህ አትጠራትም፤ ስሟ ከዛሬ ጀምሮ ሣራ ይሁን።

ዘፍጥረት 17፡15 (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

በጥሪህ ውስጥ ተመላለስ። የእምነት ጉዞን ቀንደኛ ጠላቶች ልታሸንፍ ይገባሃል። በአገልግሎትህ ውስጥ ፍርሃትና ማስፈራራት ወደ ፍሬያማነት አይመሩም።

## 4. ፍሬያማነት ለወጣቶች ብቻ ቢመስልም ወደ ፍሬያማነት የሚወስድህን ተግባራዊ እርምጃ ውሰድ።

ሣራም ፀነሰች፤ ... ለአብርሃም በእርጅናው ወንድ ልጅን ወለደችለት። አብርሃምም ... ልጁን ይስሐቅ ብሎ ጠራው።

ዘፍጥረት 21፡2-3

ዳግም እንደገና፡- ጠቃሚ፣ ቀናኢ፣ በስሜት የተሞላ፣ የሚደነቅ፣ ኃይል የተሞላ እና የሚጠቅም ለመሆን ወስን። ይህ በአገልግሎትህ ላይ ያለውን የመካንነት መተትና እርግማን ይሰብራል።

ሣራ በዘጠና ዓመቷ ከባልዋ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጸመች። በሕይወትህ ላይ ማንኛውም ዓይነት ትንቢት ይነገር፣ ልታደርገው የሚገባህ አንድ የሆነ ነገር ይኖራል። ይስሐቅ እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ መለኮታዊ በሆነ መንገድ አልተረገዘም። ይስሐቅ የተረገዘው ቀጥተኛ በሆነው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው። ሣራ ልብሷን አውልቃ እንዲት ወጣት ሴት ከወጣትነት ባልዋ ጋር እንደምትሆነው ማድረግ ነበረባት። አብርሃምና ሣራ በዘጠናዎቹ ዕድሜ ውስጥ ሆነው በግብረ ሥጋ ግንኙነት መደሰት ነበረባቸው። እንዲት የዘጠና ዓመት፣ የወር አበባ ማየት ያቆመች ሴት እንደገና እንደ ወጣት ሙሽራ ትሆናለች ብለህ ታስባለህ?

አንዳንድ አገልጋዮች በጣም እንዳረጀ ሰው ያስባሉ፣ ይሆናሉ። በአገልግሎት ውስጥ የተወሰነ ወጣትነት ያስፈልጋል። ወጣትነት ለፍሬያማነት ያስፈልጋል።

## የመላመድን መካንነት ተዋጋ

መላመድ የመቀባት ትልቁ እንቅፋት ነው። ቤተ ክርስቲያን ለመትከል እና ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት የሚያስፈልገው ቅባት እንዳይፈስ ይከለክላል። አገልግሎት መንፈሳዊ ነገር ነው፣ መንፈሳዊ መርሆችን መታዘዝ ካልተቻለ፣ አገልግሎት ይደርቃል ውጤቱም መካንነት ይሆናል።

ሜልኮል የመካን አገልግሎት ምሳሌ ነች። ሜልኮል ባልዋን በመላመዷ ምክንያት መከራ ደረሰባት። ስለዚህም የተቀበለችው ዋጋ መካንነት ነበር። ብዙ ሰዎች ከእግዚአብሔር ሰዎች ጋር በጣም ከመላመዳቸው የተነሣ በአገልግሎት ውስጥ መካን ይሆናሉ።

> ዳዊትም ቤተሰቡን ሊመርቅ ተመለሰ። የሳኦልም ልጅ ሜልኮል ዳዊትን ለመቀበል ወጣችና፦ ምናምንቴዎች እርቃናቸውን እንደሚገልጡ የእስራኤል ንጉሥ በባሪያዎቹ ቆነጃጂት ፊት እርቃኑን በመግለጡ ምንኛ የተከበረ ነው! አለችው ዳዊትም ሜልኮልን፦ በእግዚአብሔር ፊት ዘፍኛለሁ በእግዚአብሔር ሕዝብ በእስራኤል ላይ አለቃ እሆን ዘንድ ከአባትሽና ከቤቱ ሁሉ ይልቅ የመረጠኝ እግዚብሔር የተባረከ ይሁን ስለዚህም በእግዚአብሔር ፊት እጫወታለሁ። አሁንም ከሆንሁት ይልቅ የተናቅሁ እሆናለሁ፤ በዓይንሽም እዋረዳለ ነገር ግን በተናገርሽው ቆነጃጅት ዘንድ እከብራለሁ አላት። የሳኦልም ልጅ ሲልኮል እስከ ሞተችበት ቀን ድረስ ልጅ አልወለደችል።
>
> 2ኛ ሳሙኤል 16:20-23



## ሁሉም ሰው ስለ መላመድ ሊያውቃቸው የሚገቡ ሰባት ነገሮች

1. መላመድ ማለት ስለ አንድን ሰው ወይም አንድ ነገር ያለህን አድናቆት፣ ክብር እና የአክብሮት ፍርሃት እስከታጣ ድረስ ስለ ሰው ወይም ነገር በጣም ማወቅ ማለት ነው። ከዚህም በተጨማሪ፣ አንድ ሰው ማክበር እስኪሳነው ድረስ የመዳፈርን ሁኔታ ያሳያል።
2. መላመድ የሜልኮል መካንነት ምክንያት ነበር
3. መላመድ አሁንም በዚህ ዘመን ባሉ ክርስቲያኖች ላይ መንፈሳዊ መካንነት ያመጣል።
4. መላመድ ከእግዚአብሔር ሰዎች የእግዚአብሔርን ኃይል እንዳንቀበል የሚያደርግ ትልቅ እንቅፋት ነው።
5. የእግዚአብሔር ስጦታ የፈሰገውን ያህል ታላቅ ይሁን፣ ከመላመድ የተነሣ ዋጋ ያጣል። ኢየሱስ ታላቅ ፈዋሽና አስተማሪ ነበር፣ ይሁን እንጂ የተላመዱት ሰዎች ከመኖራቸው የተነሣ ዋጋ አጥቶ ነበር።

> ከዚህም በኋላ ኢየሱስ ከዚያ ተነስቶ ወደ ገዛ አገሩ ሄደ፤ ደቀመዛሙርቱም ተከተሉት። ሰንበትም በደረሰ ጊዜ፤ በምኩራብቸው ያስተምር ጀመር፤ የሰሙትም ብዙ ሰዎች፣ ተደነቁ። እነርሱም እንዲህ አሉ፤ "ይህ ሰው እነዚህን ነገሮች ከየት አገኛቸው? ይህ የተሰጠው ጥበብ ምንድር ነው? ደግሞም እነዚህ ታምራት እንዴት በእጁ ይደረጋሉ፤ ይህ በናጢው አይደለምን? የማሪያም ልጅ፤ ... ከዚህም የተነሣ ተሰናከሉበት፤ ... እዚያም በጥቂት ሕመምተኛ ላይ እጁን ጭኖ ከመፈወሱ በስተቀር ምንም ታምራት ሊሠራ አልቻለም።"
>
> ማርቆስ 6:1-3,5
>
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ይህ ክፍል ኢየሱስ በገዛ አገሩ ታምራት ማድረግ አለመቻሉን ያሳየናል፡፡ በደንብ ስለሚያውቁት እንደ እግዚአብሔር ልጅ ሊቀበሉት አልቻሉም፡፡ ስለ ወላጆቹ፣ ስለ ቤተሰቦቹ እና ስለ ማንነቱ ጥያቄ ነበረባቸው፡፡

6. በጨለማ የእሳት ዐምድ በቀን የደመና ዐምድ ያዘዘው ሙሴ የገዛ እኅቱን ማሪያምን ሊያስደንቅ አልቻለም፡፡ ስለ ጋብቻው ተቸችው እና ለዚህም መከራን ተቀበለች፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ልቤ ለተላመዱኝ ሰዎች ዝግ ነው፡፡ በቀላሉ ከእነርሱ ጋር እንደልቤ አልሆንም፡፡ የመላመድ ችግር ያለባቸው ሰዎች ልብ ውስጥ ያሉ ጥያቄዎችን እንዲሁ አውቃለሁ፡፡

7. መላመድ የተቀቡ ሰዎችን አገልግሎት መንገድ ይቆርጣል፡፡ አብረዋቸው ከሚያገለግሉ፣ ከጓደኞቻቸው፣ እና ከቤተሰባቸው ያርቃቸዋል፡፡ እነኚህን የተቀቡ ሰዎች ወዳልተላመዱዋቸው፣ ወደ ተረሱ ድሆች እና ወደ ተተውት ይወስዳቸዋል፡፡ የዚህን ጊዜ ነው በውጭ ያሉት የሚገቡት፡፡ በውጭ ያሉት ብዙውን ጊዜ የሚገቡት የተቀቡ ሰዎችን በጣም የተላመዱትን ለመተካት ነው፡፡

## ብዙውን ጊዜ ከመላመድ የተነሳ የሚመጣውን መከራ የሚቀበሉ አራት ዓይነት ሰዎች

### 1. የሥራ ባልደረቦች

አብዛኛውን ጊዜ የመላመድ ገፈት ቀማሾች በቅርብ የሚውቁህ ሰዎች ናቸው፡፡ የሕክመና ተማሪ በነበርሁበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያኔን ስጀምር፣ ከእኔ ሊቀበሉ የቻሉ በጣም ጥቂት የሆኑ ባልደረቦቼ ብቻ ነበሩ፡፡ እኔን በጣም ከማውቃቸው የተነሳ በልባቸው፤ "ይህ ዳግ አይደለምን? እርሱንም የሚማርበትንም ክፍል እናውቃለን፡፡ ባለፈው ሳምንት ፈተና ሲንደፋደፍ አይተነዋል፡፡ ሲወድቅና ሲያልፍ እናውቃለን! እንዴት ይህ ቀጭን ጠውላጋ ልጅ ራሱን መጋቢ ብሎ ይጠራል?" ይሉ ነበር፡፡



### 2. ዘመዶች

ዘመዶች የመላመድ መከራ ቀማሾች ናቸው፡፡ እንዲህ ይላሉ፣ "ይህ የአዞያዞ(የአባቱ ቅፅል ስም) ልጅ አይደለምን? በልጅነቱ አቅፌን አሳድገነዋል፡፡" እንዲህ በማለት ይጠይቃሉ፣ "ታስታውሰኛለህ? የሁለት ዓመት ልጅ ሳለህ እሸክምህ ነበር፡፡" "አባትህን በደንብ አውቀዋለሁ"፣ ይላሉ፡፡

በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ፣ ሰዎች እንዴት እንደ እግዚአብሔር ሰው ሊቀበሉኝ ይችላሉ?

### 3. የመጋቢዎች ሚስቶች

የመጋቢዎች ሚስቶች በአብዛኛውን ጊዜ በከፍተኛ ሁኔታ በመላመድ ይሠቃያሉ፡፡ ልክ እንደ ሚልኮል፣ ሁሉም ሰው ሲደነቅ፣ እነርሱ በባሎቻቸው አይደነቁም፡፡ "አውቅሃለሁ"፣ "ማንም እንደኔ አያውቅህም"፣ "አንዳንድ ነገሮችን ልነግርህ የምችል እኔ ብቻ ነኝ"፣ "እኔ እንደነዚያ ቢሮ ውስጥ እንደሚያሞጋግሱህና ጎሽ ጎሽ እንደሚሉህ ሰዎች አይደለሁም!"፣ "ሰዎች ማንነትህን ቢያውቁ ኖሮ፣ ይደንቃቸው ነበር"፣ "ማንም ሰው እውነተኛውን ማንነትህን አያውቅም፡፡" እነኚህን የመሳሰሉትን ነገሮች ይላሉ፡፡

በአንድ በኩል፣ ስለነኚህ ነገሮች ትክክል ናቸው፣ እውነታው ግን የመላመድ ተጠቂዎች መሆናቸውም ነው!

### 4. የቅርብ ጓደኞች እና አጋሮች

እነኚህ ሰዎች መላመድ ይደርስባቸዋል፡፡ ለረጅም ጊዜ አብረውህ ቆይተዋልና የገጠሙህን ውጣ ውረዶች አይተዋል፡፡ ሹልክ ብሎ ወደ መላመድ መንሸራተት ቀላል ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ አንድን ሰው ላለመላመድ ያንን ሰው በቅርብ አለማወቅ ይሻላል፡፡

መላመድ ታማኝ አለመሆንን ይወልዳል። መላመድ ይሁዳዎችን ፈጥሯል። ይሁዳዎች የሚያሳየው፣ "የምታምንበት የቅርብ ወዳጅ" የሚባሉ ሰዎችን ነው። ሰዎች ሲላመዱ፣ አክብሮት ይጠፋባቸውና በፍጹም ማለፍ የማይገባቸውን ገደብ ያልፋሉ። መላመድ ሰዎች በፍጹም ማለት የማይገባቸውን ነገሮች እንዲናገሩ ያደርጋቸዋል።

ሜልኮል በዳዊት ላይ ስትናገር፣ በእግዚአብሔር የተቀባው ላይ የሚነሡ ዐመፀኞችና ተቃዋሚዎችን ጫማ ነው ያጠለቀችው፤ ለእግዚአብሔር እንደ ልቡ የሆነን ሰው ነው የነቀፈችው። ዳዊት የማደሪያውን ድንኳን የገነባ ሰው ነበር ግን አልተደነቀችበትም። እግዚአብሔር "እንደ ልቤ የሆነ ሰው" ብሎ የጠራውን ሰው፣ ሚች የሆነች እርሷ ግን ናቀችው። አስበው እግዚአብሔር የተደነቀበትን ሰው አንተ ሳትደነቅበት ስትቀር። አይገርምም?

መላመድ አብዛኛውን ጊዜ የሚመነጨው ከቅናት እና ከሥጋዊነት ነው። ሜልኮል የዳዊትን አገልግሎት የሚያደንቁ በመሰላት ቆነጃጂት ቀንታ ነበር። ዳዊት በእነኚ ልታይ ልታይ በሚሉ ቆነጃጂት መሳቡን አልወደደችውም።

> **ዳዊትም ቤተ ሰቡን ሊመርቅ ተመለሰ። የሳኦልም ልጅ ሜልኮል ዳዊትን ለመቀበል ወጣችና፦ ምናምንቴዎች እርቃናቸውን እንደሚገልጡ የእስራኤል ንጉሥ በባሪያዎቹ ቆነጃጅት ፊት እርቃኑን በመግለጡ ምንኛ የተከበረ ነው! አለችው።**
>
> **2ኛ ሳሙኤል 6:20**

ማርያም ሙሴን ስትተች፣ በእግዚአብሔር የተቀባ መሆኑን ከቶውንም ዘንግታ ነበር። ወደ ሥጋዊነት በመመለስ ታማኝ ያልሆነ ዐመፀኛ ሆነች።



> **ሙሴም ኢትዮጵያዊቱን አግብቶአልና ባገባት በኢትዮጵያዊቱ ምክንያት ማርያምና አሮን በእርሱ ላይ ተናገሩ**
>
> **ዘኁልቁ 12:1**

ይሁዳ ከፍተኛው የክሃዲ ዓይነት ነው። በመላመድ ስመታለል ራሱን አሳልፎ በመስጠት ከፍተኛውን ዋጋ ከፈለ።

> **እንጀራዬን ተካፍሎ የበላ የምተማመንበትም የቅርብ ወዳጄ በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣ።**
>
> **መዝሙር 41:9**
> **(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)**

## ልምድ ያልታከለበት እውቀት

በሕይወት ዘመኔ በተለያዩ ጊዜዎች የተለያዩ ሰዎች ሲቀርቡኝ አይቼአለሁ። አንዳንድ ጊዜ ሁኔታዎች ሰዎችን ከእግዚአብሔር ሰዎች ጋር የቀረቡ እንዲሆኑ ያደርጉዋቸዋል። በእነኚህ ሁኔታዎች ውስጥ፣ ሰውየው በቀላሉ ሊላመድ ይችላል። ላለመላመድ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ያስፈልጋል። በሕይወቴ እና በአገልግሎቴ ውስጥ ሰዎች ትንሽ እድል ሲሰጣቸው እንዴት ከሚገባው በላይ እንደሚላመዱ አስተውያለሁ። እስቲ የመላመድን ፍቺ ላስታውስህ።

መላመድ ማለት፣ 'አንድ ሰው ወይም አንድን ነገር ልትሰጠው የሚገባህን አድናቆት፣ ክብር፣ እና የአክብሮት ፍርሃት እስከታጣ ድረስ ማወቅ ማለት ነው። በተጨማሪም ደግሞ አንድ ሰው አክብሮት እስኪያጣ ድረስ በራሱ የሚተማመንበትን ልበ ሙሉነቱን ያሳያል።'

አንድ ቀን፣ አንዲት ወጣት ሴት በትዳሯ ውስጥ ችግር ነበረባት። ባሏ፣"ለቢሾፕ እናገርብሻለሁ" አላት። እርሷም ስትመልስለት "ግድ የለኝም። እርሱም ችግር አለበት።" አለች።

ይህን ስሰማ ፈገግ አልሁ፡፡ መላመድ አንገቱን ቀና እያደረገ እንደሆነ አወቅሁ፡፡ ምናልባትም ይህችን ሰው ጥቂት ቀናት በቤታችን እንድታሳልፍ በመፍቀዴ አጥፍቼ ሊሆን ይችላል፡፡
በሌላ ጊዜ ደግሞ፣ ጥቂት ቀናት በቤታችን ውስጥ ያሳለፈች አንድ ዘመድ የሆነ ችግር አጋጠማት፡፡ የምክር አገልግሎት ከሰጠኋት በኋላ፣ ያካፈልኳትን ነገር የተረዳች መሰለች፡፡ የተባረከች መስላ ምስጋና አቀረበችልኝ፡፡

የሚያሳዝነው ግን፣ የእውቀት ሰው እንጂ የተግባር ሰው አይደለም፣ እንዳለችኝ ሰማሁ፡፡ ምን ማለቷ ነው፣ እርሷ የገጠማትን ዓይነት ችግር ገጥሞኝ የማያውቅና ስለዚህም ደግሞ ምክሬ ከንድፈ ሐሳብነት የማያልፍ ነው ማለት ነው፡፡

እንዲህ ስል አሰብሁ፣ "ዛሬ ልምድ የሌለው የእውቀት ሰው ሆንሁ፡፡ እንዲህ ሊሆን የቻለው ይህችን ሰው ከቤተሰቤ እና ከእኔ ጋር በጣም እንድትቀርብ በመፍቀዴ ብቻ ነው፣ እንዲህ ዓይነት አስተያየት ልትሰጥ የቻለችው፡፡"

አንዳንድ ጊዜ ከአንድ ሰው አገልግሎት ያለመቋረጥ መቀበል እንድትችል ከሩቅ ብታውቀው ይሻላል፡፡ ከመጋቢህ ጋር በጣም ከተላመድህ፣ በስህተት የእውቀት ሰው እንጂ የልምምድ ሰው እንዳልሆነ አድርገህ ልታየው ትችላለህ፡፡

## የመላመድህን ደረጃ ገምግም

ከእግዚአብሔር ሰው ጋር ባለህ ግንኙነት ውስጥ፣ እየተላመድኸው ነውን? የሚከተሉትን ምልክቶች ምን ያህል እንደተላመድከው እንድታውቅ ይረዱሃል፡፡ መላመድ ከፍተኛው "ቅባትን ገዳይ" እንደሆነ አስታውስ፡፡ የእግዚአብሔርን ስጦታ ዋጋ የሚያሳጣ ከፍተኛ ኃይል አለው፡፡



# የመላመድ አሥራ ሁለት ምልክቶች

## 1. አብዛኛውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከኋላ መቀመጥ

ስለ መጋቢውና ስለ ስብከቱ መግረክና መደነቅ ስታቆም ተላመድኸው ማለት ነው፡፡ ወደፊት ጠጋ ለማለት አትፈልግም፡፡ የተላመዱ ሰዎች ወደ ኋላ ተቀምጠው ከሩቅ ይመለከታሉ፡፡

አንድ ጊዜ የኬኔት ሀገንን ኮንፍረንስ በቱልሳ ኦክላሆማ ውስጥ ተካፈልሁ፡፡ አዳራሹ ውስጥ ስገባ፣ አስተናባሪው የኋላ ወንበር ሊሰጠኝ ሞከረ፡፡

እንዲህ ስለ አሰብሁ፣ "እንዴት ኬኔት ሃገን እየሰበኩ እኔ ከኋላ እቀመጣለሁ? በተቻለኝ መጠን መጠጋት እፈልጋለሁ!" ከአስተናባሪው ጋር ተደራድሬ እንዲያውም ጓደኛ አደረግሁት፡፡

እንዲህ አልሁት፣ "ጌታዬ ከየት እንደመጣሁ አታውቅም፡፡" ቀጠል በማድረግም "ዛሬ እዚህ ለመገኘት በሺዎች የሚቆጠሩ ማይሎች ተጉዤ ነው የመጣሁት፡፡ በተቻለኝም መጠን መቅረብ አለብኝ፡፡ ፎቅ ላይ የምቀመጥበት ወይም ኋላ የምቀመጥበት ምክንያት የለም፡፡"

እርሱም ተረዳኝና መንገዱን አበጀሁ፡፡ በማይታመን ሁኔታ፣ በሁለተኛው ረድፍ ተቀመጥሁ፡፡ ኬኔት ሀገን እየሰበኩ እኔ በተቀመጥኩበት በኩል ሲያልፉ እጅግ እደነቅ ነበር፡፡

ታያለህ፣ ስትላመድ፣ የእግዚአብሔርን ሰው ከቅርብም ሆነ ከሩቅ ማየትህ ምንም አይመስልህም፡፡

በኋላ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ጋር ውይይት አደረግሁ፡፡ ከተማሪዎቹ ጋር ችግር ይኖረባቸው እንደሆነ ጠየቅሁት፣ ይድንቅህ ብሎ ነገረኝ፡፡ ዋነኛው ችግራቸው መላመድ ነበር፡፡ እንዲህ

አለኝ፣ "እንደዚህ ባለ ትልቅ ኮንፈረንስ ላይ የማይመጡ አንዳንድ ተማሪዎች አሉ።" "እኚህ ሰው ታላቅ ነቢይ ናቸው እና ከእርሳቸው ለመቀበል ሰዎች ከዓለም ዙሪያ ይመጣሉ። እዚህ ግን፣ መንገዱን ተሻግረው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊመጡ የማይፈልጉ ተማሪዎች አሉ"፤ ሲል በሐዘን ገለጸልኝ። አየህ፣ መላመድ ንቀትን ይወልዳል። መላመድ ማለት አንድን ሰው በደንብ ማወቅ ማለት ነው። ይህ ደግሞ ለዚያ ሰው ያለህን አድናቆትና አክብሮት እንድታጣ ያደርግሃል።

## 2. ማዛጋት

ማዛጋት ባብዛኛው የመሰልቸት ምልክት ነው። የተላመደ ሰው በትእቢትና በአላዋቂነት የሚቀጥለው ምን እንደሆነ አውቃለሁ የሚል ነው። ብዙውን ጊዜ፣ ቃሉ ሲሰበክ የሚያዛጉ ሰዎች፣ "ይህን ስብከት አውቀዋለሁ፣ ከዚህ ቀጥሎ የሚከተለውን አውቃለሁ። የሀሳቡን ቅደም ተከተል አውቃለሁ። ይህ ሰው የሚናገረው አዲስ ነገር የለውም " ማለታቸውም ነው። ይቅር ይበለን!

## 3. እየተሰበከ መተኛት

እንቅልፋችን የሚመጣው ሲደክመን ነው። አንዳንድ ጊዜ ግን ከመደጋገምና ከመሰልቸት የሚመጣ ነው፣ የእግዚአብሔር ሰው ሲሰብክ ካልቻለ፣ ሲሰብክ ልትተኛ ትችላለህ።

## 4. የስብከት ካሴቶችን አለመግዛት እና አለማዳመጥ

የስብከት ካሴቶችን የሚያዳምጥ ሰው የመጋቢውን ድምጽ አልተላመደም። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ይህን የሚያየው መጋቢው በማይኖርበት ጊዜ እንኳ ያለማቋረጥ በእርሱ መባረክ እንደሆነ ነው። ለምን የስብከት ካሴቶች መግዛት እንዳቆምህ ራስህን ጠይቀህ ታውቃለህ? ምናልባት መልሱ መላመድ ሊሆን ይችላል።



## 5. መሪህ በሆነው የእግዚአብሔር ሰው የተጻፉ መጽሐፍትን አለመግዛት እና አለማንበብ

መጽሐፎቼን ለመግዛት ሰዎች ከሩቅ ሲመጡ እመለከታለሁ። ሰዎች ብዙ ማይል ተጉዘው በመምጣት በርካታ መጽሐፍቶቼንና የስብከት ካሴቶቼን በመግዛት በጉጉት የሚያነቡበትና የሚያዳምጡበት ጊዜ አለ። የሚደንቀው ግን የራሴ ቤተ ክርስቲያን አባሎች አብዛኛውን ጊዜ እኚህን መጽሐፍቶችና ካሴቶች አልፈው ከዚያ ይልቅ ምግብና ለስላሳ ያዛሉ። መላመድ የመደነቅ እና የመሳብ ስሜትህን ያሳጣሃል።

## 6. ስለ እግዚአብሔር ሰው ማንነት ማውራት

በመሠረቱ ሁሉ የእግዚአብሔር ሰው፣ "ሰው" ነው። ሰው እስከሆነ ድረስ፣ ሰዎች በሚያልፉበት ሁሉ ያልፋል። ማንም በእግዚአብሔር የተመረጠ ሰው ፍጹም የሆነ ሕይወት ኖሮት አያውቅም። ያሳለፈው ታሪክ አለው! ቤተሰብ አለው። ውድቀቶች አሉት። ፍጹም ያልሆነ ትዳር አለው። እንደማንኛውም ሰው ተግዳሮቶች አሉት። ከተፈጥሮአዊ የሕይወት ገጽታዎች አንዱን በማንሣት ማጣጣል ቀላል ነው። ስለ እግዚአብሔር ሰው ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ አንሥቶ ማውራት ለእርሱ ያለህ አድናቆት እንደጠፋብህ የሚያሳይ እርግጠኛ ምልክት ነው። ይህ በእርግጠኛነት የእርሱ ቅባት በሕይወትህ ላይ የሚያመጣውን ውጤት የሚደመስስ ነው።

## ቱሞስ(THUMOS) እና ኤክፕሌሶ(EKPLESSO)

ኢየሱስ በገዛ አገሩ ሲሰብክ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በሉቃስ 4:28 ላይ፣ ". . . ይህን ሰምተው ቁጣ ሞላባቸው" ይላል። ቁጣ የሚለው ቃል በግሪክ ቱሞስ(THUMOS) ነው፤ ቅሬታ በአእምሮ ውስጥ እየፈላ ሲመጣ ማለት

ነው፡- መጋል፣ ትንፋሽ እስኪያጥርህ ድረስ መናደድ እና ቁጣ ማለት ነው። የተሳመዱት ሰዎች በኢየሱስ ስብከት ተቆጡ።

በገሊላ ሲሰብክ በሉቃስ 4:32 ላይ በተገለጸው መሠረት ". . .በትምህርቱ ተገረሙ" ይላል። " 'ተገረሙ' ከግሪኩ 'ኤክፕሌሶ' (EKPLESSO) " የተወሰደ ሲሆን መገረም፣ መደነቅ እና በፍርሃት መመታት ማለት ነው።

ልብ በል፣ በቱሞስ እና ኤክፕሌስ መካከል ያሉት ጥቅሶች አራት ብቻ ናቸው። አስተውል፣ በተጨማሪም 'ቱሞስ' (ቁጣ) የሆነው በኢየሱስ አገር በናዝሬት ሲሆን፣ 'ኤክፕሌሶ' (አድናቆት) የሆነው ደግሞ ከኢየሱስ አገር ሁለት መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው በገሊላ ነው።

## 7. የእግዚአብሔርን ሰው ቤተሰብ ጉዳይ ማውራት

> **ይህስ ጸራቢው የማርያም ልጅ የያዕቆብም የዮሳም የይሁዳም የስምዖንም ወንድም አይደለምን? እህቶቹስ በዚህ በእኛ ዘንድ አይደሉምን? አሉ ይሰናከሉበትም ነበር።**
>
> **ማርቆስ 6:3**

ይህን በማድረግ፣ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ካለው ተአምራት ራስህን ትቆርጣለህ። ኢየሱስ ወደ ገዛ አገሩ በሄደ ጊዜ፣ በማንነቱ ዙሪያ ብዙ ውይይት ሲካሄድ ነበር። አንዱ ሰው፣ "ያንን ልጁ አውቀዋለሁ፣ የእኅቴ ልጅ ነው። እርሱና አባቱ ለብዙ ዓመታት ቁም ሳጥኔን ይሠሩ ነበር።" ይል ነበር።

በከተማው ውስጥ ካለው መላመድ እና ጥርጣሬ የተነሣ ኢየሱስ እጅግ አነስተኛ የሆነ ተአምራት ብቻ አደረገ። መላመድ ከበረከትህ እንዲለይህ አትፍቀድ።



## 8. ስሕተት መፈለግ እና ስሕተትን ማጉላት

ስለምታከብራቸው ታላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች በምታስብበት ጊዜ ሁሉ፣ ብዙውን ጊዜ ስለ ስሕተታቸው አታስብም። ተጋባዥ ሰባኪ ሲኖር፣ ትዕግሥት የለሽ ቢሆን ወይም በቀላሉ የሚቆጣ ቢሆን ግድ የሚሰጠው ሰው የለም። ዕዳ ይኑርበት ወይም አባካኝ ይሆን ብሎ ማንም አያስብም። የምናደርገው ነገር ቢኖር የዚህን የእግዚአብሔር ሰው አገልግሎት መቀበል ነው።

ይሁን እንጂ፣ ስለ ለመድናቸው የእግዚአብሔር ሰዎች የምናስባቸው ሐሳቦች እነኚህ ናቸው። "ዛሬ ሳይናደድ አይቀርም፣ ይህ ሰው ትዕግሥት የለውም ብለን እናስባለን።" እየሰበከ ሳለ ለራሳችን እንዲህ እንላለን፣ "የሚለው ገብቶናል፣ ለምን ወደሚቀጥለው ነጥብ አያልፍም?"

አስታውሳለሁ ከዓመታት በፊት፣ **በመልእክቱ ደስ የምትሰኝ አንድ አባል ነበረችኝ**። ስለ እኔ በጣም ጥሩ አስተማሪነት ለብዙ ሰዎች በመንገር የቤተ ክርስቲያኔ አባል እንዲሆኑ አድርጋለች። ይሁንና ጊዜው ሲገፋ፣ ስብከቴን እና እኔን እየተላመደች መጣች።

አንድ ቀን ከቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም በኋላ እንዲህ አለችኝ፣ "እንደሚመስለኝ ያለፈውን ሳምንት ስብከት በመከለስ ብዙ ሰዓት ወስደሃል።" ቀጠል አድርጋም፣ "ስለዚህ ዛሬ ላስተማርካቸው ነጥቦች የነበረህ ጊዜ በጣም አጠረ።"

ከጥቂት ሳምንቶች በኋላ፣ ሌላ አስተያየት ሰጠች፣ "በስብከትህ ውስጥ ድግግሞሽ ይበዛል።" ከዚህ በኋላ በምሰብክበት ጊዜ ሁሉ ፊቷን አኮሳትራ እመለከታለሁ። ይህች ሴት ቀስ በቀስ ቤተ ክርስቲያን መምጣቷን አቆመች።

ምናልባት ትክክል ትሆን ይሆናል፣ ግን ያልተረዳችው ነገር፣ የምሰብከው ባለፈው ሳምንት ላልነበሩትና በዚህ ሳምንት ለመጡ ሰዎች ነው። በየሳምንቱ የሚኖረኝ ጉባዔ አዲስ ነው ለማለት ይቻላል። ስሕተቶች ሊኖሩብኝ ይችል ይሆናል፣ ግን እግዚአብሔር ከእነርሱ ይልቅ በእኔ ሠርቷል።

በዓይንህ ውስጥ ያለውን ግንድ አውጥተሃል? ለምን በመጋቢህ ዓይን ውስጥ ያለው ጉድፍ ላይ ታተኩራለህ? መላመድ ተቺ እንድትሆን አድርጎሃል።

## 9. የእግዚአብሔርን ሰዎች መገምገምና ደረጃ መስጠት

ዲሞክራሲ በመሠረታዊ ተፈጥሮ፣ መሪዎቻችንን ያለማቋረጥ እንድንገመግም ጥሪ ያደርግልናል። ይህ ነው ለትክክለኛው ሰው ድምጽ እንድንሰጥ የሚያደርገን። የሚያሳዝነው ግን፣ ብዙዎች ይህን ልምምድ ወደ ቤተ ክርስቲያን እናመጣለን ብለው ሲያስቡ ይስታሉ።

አንድ ቀን ከቤተ ክርስቲያን መልስ ወደ ቤቴ ስመጣ አንድ ሰው መኪና ውስጥ አንድ ጥያቄ ጠየቀ። "ስብከቱን እንዴት አገኛችሁት?" ብሎ ጠየቀ።

ለጥቂት ደቂቃዎች መኪናው ጸጥ ካለ በኋላ አንድ ሰው እንዲህ አለ፣ "ምንም አይልም፣ 70% ሰጥቼዋለሁ።"

ከዚያም አንድ ዕድሜው ገፋ ያለ ሰው፣ "አይ አይ አይሆንም። የሚገባው 49% ነው።" አለ።
ሌላው ሰው፣"ለምን 49% መልእክቱ በጣም መጥፎ ነበር?" ብሎ ጠየቀ።
ለራሴ፣ "ይህ ምስኪን መጋቢ በጉባዔው እየተገመገመ ነው።" ብዬ አሰላሰልሁ።



## 10. የእግዚአብሔር ሰውን ምክር አለማመን

አንድን ሰው ትልቅ ዋጋ ስትሰጠው፣ ለሚሰጠው ማንኛውም ዓይነት ምክር ከፍተኛ ዋጋ ትሰጣለህ። መላመድ ሲመጣ፣ ምክርን መቀበል ይበልጥ አስቸጋሪ እየሆነ ይመጣል። ምክር በተሰጠ ቁጥር ምክሩን ላለመቀበል ምክንያት ይኖራል።

## 11. ለቅባቱ አክብሮት አለመስጠት

እየተላመድህ ስትመጣ፣ ከእግዚአብሔር ሰው ጋር መንፈሳዊ ግንኙነት ማድረግህን ታቆማለህ። መቀባቱ እንኳ ትዝ አይልህም። የምታየው ነገር ተፈጥሯዊ ብቻ ይሆናል። ተፈጥሯዊ ማንነቱን የምትመለከት ከሆነ የምታየው ደካማ ጎኑን ነው። አታከብረውም፣ አመለካከትህ ይበላሻል።

> የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው። **በመበስበስ** ይዘራል፣ ባለመበስበስ ይነሣል፣ **በውርደት** ይዘራል፣ በክብር ይነሣል፣ በድካም ይዘራል፣ በኃይል ይነሣል፣
> 1ኛ ቆሮንቶስ 4፡42-43

የአገልግሎት ቅባት ከአንድ የእግዚአብሔር ሰው ወደ ሌላው ሰው ይተላለፋል። ቤተ ክርስቲያን የመትከል ቅባት ከአንድ ሰው ወደ ሌላው ሰው ይተላለፋል። ኤልሳዕ ከኤልያስ ጋር የነበረው ግንኙነት ጥሩ ምሳሌ ነው። "አባቴ" ብሎ እየጠራው ለብዙ ዓመት ያገለግለው ነበር። ከመቅረቡ የተነሣ ለቅባቱ ያለው አክብሮት አልጠፋም። ታላቅ ከሚባሉት ቅባቶች ውስጥ የሆነውን ቅባት በእጥፍ ለመቀበል ቻለ።

ሁሉም ሰው የመላመድ ገፈት ቀማሽ አይሆንም። አንዳንድ ሰዎች ለቅባቱ ያላቸው ከፍተኛ አክብሮት ሳይቀንስ የቅርብ ሰው ሆነው መቀየት ይችላሉ። ለብዙ ዘመን አብረውኝ የቆዩ እና "ድካሜን"፣ "ውርደቴን"፣ እና "ውድቀቴን" ያዩ ግን በሕይወቴ ላይ ያለውን የእግዚአብሔር መገኘት፣ ፍርሃት፣ መማረክ እና አክብሮታቸውን የጠበቁ ሰዎች አሉ። ኤልሳዕ ለብዙ ዓመታት ያደረገው ይህን ነው። እናም በኤልያስ ላይ ያለውን ቅባት በእጥፍ ተቀበለ። በእግዚአብሔር ሰዎች ላይ ባለው ግልጽ

## 12. የአንተ የሆነውን የእግዚአብሔር ሰው አለማክበርና አለማድነቅ

መጋቢህን ስትለምደው፣ በቀላሉ ችላ ልትለው ትችላለህ። ብዙውን ጊዜ የተላመድናቸውን ሰዎች ችላ እንላቸዋለን።

አንድ በጉባዔው ፈጽሞ ተከብሮ የማያውቅ መጋቢ አስታውሳለሁ። ቤተ ክርስቲያኑ ሁልጊዜ አንድ ተጋባዥ የሆነ ሰባኪን ያከብር ነበር። ይህ ሰባኪ በሚመጣበት ጊዜ ብዙ ሕዝብ ይመጣና ለዚህ ተጋባዥ ሰባኪ አድናቆቱን ይገልጽ ነበር። ገንዘብና ስጦታ በማምጣት ይህን ተጋባዥ ሰባኪ ያደንቁ ነበር። ቤተ ክርስቲያኒቱ ግን በፍጹም የራሷን መጋቢ አክብራ አታውቅም። እዚህ ጋር ያለው ሽንገላ ተጋባዡን በእግዚአብሔር እንደተላከላቸው አድርጎ ማሰብ ነበር። እውነታው ግንስለ እነርሱ በፍቅር የሚደክም የለመዱት መጋቢያቸው ነው።

እኔ ለቤተ ክርስትያኔ አባላት የእግዚአብሔርን ሰው ማክበርና ስጦታ መስጠት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆነ አስተምራለሁ። ይህ የእግዚአብሔርን ሰው ኑሮ ለማሻሻል ሳይሆን የእግዚአብሔርን ስጦታ ለማክበርና የመላመድን መንፈስ ለመግደል ነው።

*ከዚህም ሁሉ በላይ፣ ልጄ ሆይ! ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም!*



*ምዕራፍ 14*

# ምልጃ ከመካንነት የመውጫ መንገድ

## የጳውሎስና የበርናባስ የቤተ ክርስቲያን የመትከል አገልግሎቶች

**በአንጾኪያም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ነቢያትና መምህራን ነበሩ እነርሱም በርናባስ፣ ኒገር የተባለው ስምዖንም፣ የቀሬናው ሉክዮስም፣ የአራተኛው ክፍል ገዥ የሄሮድስም ባለምዋል ምናሔ፣ ሳውልም ነበሩ። እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ፦ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ። በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለዩም እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው። እነርሱም በመንፈስ ቅዱስ ተልከው ወደ ሴሌውቅያ ወረዱ ከዚያም በመርከብ ወደ ቆጵሮስ ሄዱ።**

**የሐዋርያት ሥራ 13፡ 1-4**

የጳውሎስ እና የበርናባስ አገልግሎቶች የተወለዱት ከምልጃ ነበር። ታላቆቹ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ተካዮች የተወለዱት ጌታን ሲያገለግሉ እና ሲጾሙ ነው። የምትጸልይ ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ ወደ አዲስ አገልግሎቶችና ወደ ቤተ ክርስቲያን እድገት ታመራለች። ከመካንነት የመውጫው መንገድ ቤተ ክርስቲያንን የመትከል መንገድ ነው። የወንጌል ስብከት መንገድ ነው።

ጽኑ ጸሎት በአገልጋዮች ሕይወት ውስጥ ሁልጊዜ ወደ ፍሬያማነት ያመራል ብዬ አምናለሁ። የምትጸልይ ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ ፍሬያማ ትሆናለች ማለት ይቻላል። እውነተኛ ጸሎት ሲጀምር ቤተ ክርስቲያናት ይተከላሉ፣ አገልጋዮች ይላካሉ።

> ተቀመጠበት፤ አሮንና ሖርም አንዱ በዚህ አንዱ በዚያ ሆነው እጆቹን ይደግፉ ነበር፤ ፀሐይም እስክትገባ ድረስ እጆቹ ጠነከሩ።
>
> ዘፀአት 17፡8-12

በአማሌቅ ላይ ድልን ያመጣው የሙሴ የተቀጣጠለ ጸሎት፣ ሌላኛው የጽናት ጸሎት ምሳሌ ነው። አማሌቅ የሚያሳየው የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያንን ከበስተ ኋላ ሆኖ የሚያጠቃ የአጋንንት ኃይልን ነው። ከአማሌቅ የሚሰነዘር ተደጋጋሚ (የማያቋርጥ) ጥቃት በእያንዳንዱ አገልግሎት ላይ ያለውን ቤተ ክርስቲያን የመትከል ፍላጎት ይገድላል። በአገልግሎት ውስጥ መነሣትና አማሌቅን በመንፈስ መፋለም ያስፈልጋል።

## የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን

የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን፣ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመሪዎቻቸው ላይ እንዲሆን በጽናት ጸለዩ።

> ተፈትተውም ወደ ወገኖቻቸው መጡና የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች ያሉአቸውን ሁሉ ነገሩአቸው። እነርሱም በሰሙ ጊዜ በአንድ ልብ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ድምጻቸውን ከፍ አደረጉ እንዲህም አሉ፦ ጌታ ሆይ አንተ ሰማዩንና ምድሩን ባሕሩንም በእርሱም የሚኖረውን ሁሉ የፈጠርህ፤ አሁንም ጌታ ሆይ ወደዛቻቸው ተመልከት ለመፈወስም እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ ብላቴናህም በኢየሱስ ስም ምልክትና ድንቅ ሲደረግ፣ ባሪያዎችህ በፍጹም ግልጥነት ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው። ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፤ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፤ **የእግዚአብሔርንም ቃል በገልጥ** ተናገሩ።
>
> የሐዋርያት ሥራ 4፡23,24,30,31

እግዚአብሔርም ጸሎታቸውን ሰማ ውጤቱንም ተመልከት። ቤተ ክርስቲያን በጽናት መጸለይ ስትጀምር ሁልጊዜ ውጤት ይኖረዋል። ጸሎት ወደፊት ሲገፋ የእግዚአብሔር ቃል ይሰበካል። የእግዚአብሔር ቃል ሲሰበክ ቤተ ክርስቲያናት ይተከላሉ።



ልዩነት የሚያመጣው የጽናት ጸሎት እንደሆነ ልናተኩርበት ይገባናል። አንዳንድ ጊዜ፣ የጸሎት ፕሮግራም አስገ የሚሉ ሰዎችን እመለከታለሁ። አንዳንዶቹ ሲተኙ ሌሎቹ ደግሞ እንዲሁ ጊዜውን ያሳልፋሉ። አንድን ሰው እያናገርኸው ቢተኛ ምን ይሰማሃል? ይህ ሰው ወይ ፈጽሞ እንደማያከብርህ ወይም ምንም ፍላጎት እንደሌለው ታስባለህ።

## የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት

ኢየሱስ የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወቱ እንዲፈጸም በጥልቅ ጸለየ።

> እርሱም በሥጋው ወራት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና እንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፤ እግዚአብሔርንም ስለመፍራቱ ተሰማለት።
>
> ዕብራዊያን 5፡7

የዚህ ማስረጃው የደም ላብ ሲያልበው ሲጀምር ነው። የጽናት ጸሎት ሁሌም ይሠራል። የኢየሱስ አገልግሎት ታላቅ ስኬት ነበር! በእነኚህ ጸሎቶች ከሁለት ሺ ዓመታት በኋላ፣ አሁንም ቤተ ክርስቲያናት እየተተከሉ ነው። መጽሐፍት እየተጻፉ ነው። ስለ ክርስቶስ ዝማሬዎች እየተቀነባበሩ ነው። ብዙ ሰዎች ለታላቁ አምላካችን አገልግሎት በፈቃዳቸው ራሳቸውን እየሰጡ ነው።

በጽናት መጸለይን ስትለምድ በአገልግሎትህ ውስጥ ታላቅ ስኬትን ታገኛለህ። ምን ማድረግ እንደሚገባህ በማታውቅበት ጊዜ ሁሉ፣ ኢየሱስ ያደረገውን አድርግ። ኢየሱስ ሲጸልይ ጮኸ! ኢየሱስ እስኪያልበው ጸልዮአል! ራስህ አንብበው!

> በፍርሃትም ሲጣጣር አጽንቶ ይጸልይ ነበር፤ ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበረ።
>
> ሉቃስ 22፡44

*ከዚህም ሁሉ በላይ፣ ልጄ ሆይ፣ ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም!*

ምዕራፍ 15

# ቃል ኪዳናት እና ቤተ ክርስቲያንን መትከል

እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅ አምላክ ነው። የእግዚአብሔርን ክንድ እንዴት ማንቀሳቀስ እንደሚቻል ያለው የመገለጥ ግንዛቤ አናሳ ነው፣ ይህን ቃል ኪዳን የመግባት ቁልፍ እሰዋለሁ።

ሐና ልጇን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ቃል ኪዳን ገባች። ማንም ሰው ልጁን ለጌታ አገልግሎት ለመስጠት ቃል ኪዳን መግባት አያስፈልገውም። ይሁን እንጂ ከጌታ ጋር ቃል ኪዳን ለመግባት መነሣሣት እግዚአብሔር መለኮታዊ በሆነ ሁኔታ እንዲባርክህ ያነሣሣዋል፤ ሐና እግዚአብሔር ማኅጸኗን ከፍቶ ልጆቿን እንዲሰጣት እነሣሣችው። አንድ ብቻ እንኳ ቢሆን መልሳ ልትሰጠው ተሳለች።

ያዕቆብ ለእግዚአብሔር በመሳል እና ትልቅ በረከት ወደ ሕይወቱ እንዲመጣ የለመነ ሌላው ሰው ነው።

> ያዕቆብም እንዲህ ብሎ ስእለት ተሳለ፡- እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን በምሄድበትም በዚች መንገድ ቢጠብቀኝ፣ የምበላውንም እንጀራ የምለብሰውንም ልብስ ቢሰጠኝ፣ … እግዚአብሔር አምላኬ ይሆንልኛል።
>
> ዘፍጥረት 28፡20,21

ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የገባ የመጨረሻው ምሳሌ ዮፍታሔ ነው።

> ዮፍታሔም፡- በእውነት የአሞንን ልጆች በእጄ አሳልፈህ ብትሰጠኝ፣ ከአሞን ልጆች ዘንድ በደህና በተመለስሁ ጊዜ ሊገናኘኝ ከቤቴ ደጅ የሚወጣው ማንኛውም ለእግዚአብሔር ይሆናል፤ ለሚቃጠልም መሥዋዕት አቀርበዋለሁ ብሎ ለእግዚአብሔር ስእለት ተሳለ።
>
> መሳፍንት 11፡30-31

ቃል ኪዳን መግባት (ስዕለት) እግዚአብሔርን በሕግ የታሰረ ስምምነት ውስጥ የምታስገባበት የጸሎት ዓይነት ነው። ብዙ ሰዎች በአገልግሎት ውስጥ ሲያከብራቸው እምነት ያጎድላሉ። ጌታ ዓመታት ባለፉ ቁጥር በታማኝነታቸው ጸንተው የሚቆዩ ሰዎችን እየፈለገ ነው። ምናልባት ለተጠራህበት አገልግሎት ሁልጊዜ ታማኝ ለመሆን የምትጸልየው የመሰጠት ጸሎት በሕይወትህ ላይ እጅግ የምትሻውን የእግዚአብሔር ጸጋ እንዲለቀቅልህ ሊያደርግ ይችላል። ለእግዚአብሔር ታማኝ የማትሆን ከሆነ ለምን ውድ የሆነውን ቅባቱን ይሰጥሃል? እነኚህን ቃል ኪዳኖች የገቡ ሁሉ ቃል ኪዳናቸውን ስለጠበቁ እግዚአብሔርም በእርሱ በኩል ያለውን ቃል ኪዳን ጠበቀ።

*ከዚህም ሁሉ በላይ፣ ልጄ ሆይ፣ ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም!*

*ምዕራፍ 16*

# የርብቃ ቅባት

## የርብቃ በረከት በአንተ ላይ እንዲሆን ትንቢት እናገራለሁ!

ይህን ምዕራፍ ስታነብ የርብቃን በረከት ተቀበል! በሕይወትህ እና በአገልግሎትህ ላይ የርብቃ ቅባት እንዲመጣ እተነቢያለሁ! በሕይወትህ እና በአገልግሎትህ ውስጥ የፍሬያማነት እና የቤተ ክርስቲያን እድገት ጸጋ እንዲለቀቅ በማመን ለራስህ ደግመህ ደጋግመህ ተናገር። በእርግጥ ይፈጸማል! በእርግጥ በመጨረሻ ይፈጸማል!

> ርብቃንም መረቁአትና፦ አንቺ እህታችን፤ እልፍ አእላፋት ሁኚ ዘርሽም የጠላቶችን ደጅ ይውረሱ አሉአት።
>
> ዘፍጥረት 24፡60

*"ርብቃንም መረቁአትና..."*

በአገልግሎት ኃይል ውስጥ እንድትኖር ባረኩህ!

*"...አንቺ እኅታችን ነሽ..."*

አንተ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ውስጥ ወንድሜና አጋሬ እንደሆንህ አውጃለሁ። ለጌታ አብረን እየሠራን ነው። በጠላት ላይ ድል ተሰጥቶናል። በእኛ ላይ የተሠራ መሣሪያ አይከናወንም። አንዱ ሺዎችን ሊዋጋ ይችላል፤ ሁለት ግን ዐሥር ሺዎችን።

"...እልፍ አእላፋት ሁኚ..."በአገልግሎት ኃይል ውስጥ ኑር! በሺዎችና በሺዎች የሚቆጠሩ መንፈሳዊ ልጆች እናትና አባት ሁን! ያብዛህ!



በሺዎችና በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በአገልግሎትህ ወደ ጌታ ሲመጡ እይ! እግዚአብሔር ለአንተ ያዘጋጀልህን ነገሮች ታያለህ!

*"...ዘርሽም የጠላቶችን ደጅ ይውረሱ..."*

በሰይጣንና በአጋንንቶች ላይ ድልን አግኝ! ከተሞችን፣ ገጠሮችን እና ዋና ከተሞችን ለክርስቶስ አሸንፍ! ውጊያው ሁልጊዜ በጠላቶች ደጅ እንጂ በፍጹም በአንተ ደጅ አይሁን!።

ተነሥና ተዋጋ፣ በዚህ ምድር ላይ የመጨረሻው ውጊያ ነውና። የገዛነም ደጆች በሰፊው ተከፍተዋል ይሁን እንጂ መንግሥተ ሰማያትም ሠራዊቱን ለቋል። የሠራዊቱ ጌታ ኢየሱስ ነውና በእርግጠኝነት እናሸንፋለን።

ብዙዎች ቆስለዋል፤ ግን ብዙዎችም ገና ብርቱዎች ናቸው! ከአመድ ላይ ተነሥ! የቆሰለውም ወደ መጨረሻው ዘመን ጦርነት ይግባ። ጌታ ብሏልና እናሸንፋለን! ጌታ ብሏልና እናሸንፋለን! ጠባሳህ በትንሣኤ ቀን የክብርህ ምክንያት ይሆናል። በዚያ ቀን፣ የጦርነቱ ቁስሎች የተከበርህ ተዋጊ ያደርጉሃል። ታማኝ ባሪያዬ የሚጠብቅህ ታላቅና የላቀ ክብር ነው!

የሚያንጸባርቁ አክሊሎችህ፣ ውብ ቤቶችህ፣ የከበሩ ድንጋዮችህ እና ሊነገሩ የማይችሉ ሽልማቶችህ ለዘላለም ተከማችተውልሃል። የድልህን ጊዜና ሰዓት ስለቆረጥሁ አትፍራ!

*ከዚህም ሁሉ በላይ፤ ልጄ ሆይ፤ ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም!*

## ምዕራፍ 17

# መሥዋዕትነትና ቤተ ክርስቲያንን መትከል

**ኢየሱስም መለሰላቸው እንዲህ ሲል፡- የሰው ልጅ ይከብር ዘንድ ሰዓቱ ደርሶአል። እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች።**

**የሐንስ 12፡23-24**

ቤተ ክርስቲያን ለመትከል የጠፋው ቅመም መሥዋዕትነት ነው። ይህ ዋና ቁልፍ መካከለኛ የሆነውን አገልግሎት ከመካንነት ወደ ፍሬያማነት ያሸጋግረዋል። መሥዋዕትነት ሹመት ብቻ ይዞ የተቀመጠውን አገልጋይ፣ ወደ እውነተኛ ፍሬያማ አገልጋይነት ያሸጋግረዋል። ቤተ ክርስቲያንን ከአንዲት ነጠላ ቤተ ክርስቲያንነት ወደ ብዙ የቤተ ክርስቲያናት ሰንሰለትነት ይቀይራታል። መጋቢውንም ወደ ቤተ ክርስቲያን ተከላ ያንቀሳቅሰዋል።

ለሞት ዝግጁ መሆን በብዙ ጥሩ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ የጠፋ ቅመም ነው። ለመሥዋዕትነት ዝግጁ የሆኑ ሰዎች እስከሌሉ ድረስ ብዙ ቤተ ክርስቲያናት ትንሽ እንደሆኑ ይቀራሉ። መሥዋዕትነት አስፈላጊ የሆነበት ጊዜ መጥቷል። መሥዋዕትነት መክፈል አለመቻል ውጤቱ መካንነት ነው።

ብዙ ቤተ ክርስቲያናት ድንበሩ ላይ ደርሰዋል። ብዙ አገልግሎቶች ብዙ ማድረግ እየቻሉ በማድረግ ላይ አይደሉም። ይህም መሥዋዕትነት መክፈል ስለማይፈልጉ ነው። የመረጃ ወይም የእውቀት ዕጦት የለባቸውም።



ብዙ ሰዎች እኔ የማውቀውን ያውቃል። መጽሐፍቴን አንብበህ ከሆነ፣ የተወሰነ እውቀት ሊኖርህ ይገባል። ይሁን እንጂ፣ እውቀት ብቻ በቂ አይደለም! እኔ ያለኝ እውቀት ቢኖርህም እኔ ያለኝ ፍሬ ሊኖርህ አይችልም። እኔ ያለኝ እንዲኖርህ፣ ዋጋ መክፈል አለብህ። ሁሉም ሰው ሊከፍል የሚገባው ዋጋ አለ። የክብር ዋጋ ለሁሉም አንድ ነው! መጽሐፍ ቅዱስ የስንዴ ቅንጣት መሬት ወድቃ ካልሞተች፣ ብቻዋን እንደምትቀር ይናገራል።

## መሥዋዕት አቅርብ፣ መሥዋዕትም ሁን

የስንዴዋ ቅንጣት በወንጌል መልእክተኛ ትመሰላለች። የወንጌል መልእክተኛ(ሚሲዮናዊ) ደግሞ ቤተ ክርስቲያናት ለመትከል የሚላክ ነው። ብቻ መሆን ማለት ደግሞ ፍሬ ቢስ መሆን ማለት ነው። አባላት ወይም ተከታዮች የሌሉት ማለት ነው። ይህ የመሞት ሂደት በእግዚአብሔር ሰው ውስጥ ቀስ በቀስ ብዙ ፍሬ ያፈራል።

ኢየሱስ በመስቀል ላይ ባይሞት ኖሮ ያፈራውን ፍሬ ባላፈራ ነበር። በመንግሥተ ሰማያት ከአባቱ ጋር ብቻ በሆነ ነበር። ባይሞትና ወደ ሲኦል ባይሄድ ኖሮ ሊያድነን አይችልም ነበር። ለራሱና ለአባቱ ተከታዮችን ለመማረክ፣ ወደ ምድር መውደቅና መሞት ነበረበት።

የስንዴ ቅንጣት ወደ ምድር ወድቃ መሞት አለበት። ዘር መሬት ላይ ሲወድቅ፣ ይፈረካከስና ይፈርሳል። ይህን ነው መሞት የምንለው። ዘሩ ፍሬ ከመሆኑ በፊት በእርግጥ የሚያልፍበት ሂደት አለ። ያ ሊሆን የሚችለው ሲጠፋና ሲሞት ብቻ ነው።

ልንጨብጠው የሚገባን እጅግ አስፈላጊ እውነት የ"ሞት"ን አስፈላጊነት ነው። ብዙ ነገሮችን የሚያውቁ ብዙ ንፁሕ መሪዎች አሉ። ብዙ ስለሰሙ በእግዚአብሔር ዘንድ በከፍታ ላይ እንደሆኑ ያስባሉ። የሚያሳዝነው እውቀት ትዕቢትን ያመጣል።

.... ሁላችን እውቀት እንዳለን እናውቃለን። እውቀት ያስታብያል። ፍቅር ግን ያንጻል።

፻ ቆሮንቶስ 8፡፣

የእግዚአብሔር መንግሥት ከታሪክና ከአስተምህሮ(ዶክትሪን) ትምህርት ቤት የበለጠ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ብዙ ምስክር ወረቀቶችን ከማግኘት የበለጠ ነው። ያለዚህ የመሞት ሂደት፣ እውቀት ምንም አይፈይድም።

አንዳንድ በጣም የተማሩ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ተንታኝ ምሁራን በእውነተኛ አገልግሎት ላይ ውጤታማነታቸው እጅግ አናሳ እንደሆነ አስተውለሃል? እንዲያውም አንዳንዴ፣ ምሁር በሆኑ መጠን እምነት የለሽ እና እግዚአብሔርን የማያውቁ እየሆኑ ይሄዳሉ።

አንዲት ቅንጣት ትልቅ ዛፍ ልትሆንና ብዙ ፍሬ ልታፈራ የምትችለው በምድር ላይ ወድቃ ስትሞት ብቻ ነው።

## የአገልግሎት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

ወጣቶችህን የመላኪያ ጊዜ ነው። በአገልግሎት የሠለጠኑትን ወደ መስክ የመላኪያ ጊዜ ነው። ጌታ ያለ ማቋረጥ ምርጦቼን እንድልክ መርቶኛል። አንድ ቀን፣ በሥሩ ብዙ የበታች መጋቢዎች ያሉት ተቀዳሚ መጋቢ፣ "የመጋቢዎቼን ብቃት እንዴት ማሳደግ እችላለሁ?"ሲል ጠየቀኝ።

"ወደ 'ሁለተኛ ደረጃ' የአገልግሎት ትምህርት ቤት ላካቸው" አልሁት። እንዲህ ብዬ ነገርሁት፣ "በሥርህ ያሉት ብዙዎቹ መጋቢዎች ገና የአገልግሎት 'አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት' ውስጥ ናቸው፤ በዚያም ለብዙ ዓመታት ቆይተዋል"። "ወደ ሚቀጥለው የአገልግሎት ደረጃ በመልቀቅ ፈንታ፣ ከአንተ ጋር እንዲቆዩ በማድረግህ በመንፈስ እንዲጠፉ አድርገሃቸዋል።"



"እነኚህ የብዙ መቶዎች መጋቢ መሆን ሲገባቸው፣ አንዳንዶቹ ጊታር ተጫዋቾች፣ ዘማሪዎች እና የቤተ ክርስቲያንህ ዲያቆናት አደረግሃቸው። በፍጹም በአገልግሎት አልገፉም።" በማለት አብራራሁለት።

ከዚህ መጋቢ ጋር ንግግሬን እንዲህ በማለት ቀጠልሁ፣ "የሰመድሃቸውን ሰዎች መላክ በጣም ያስቸግራል፤ የምትወዳቸውን ሰዎች መላክ ያስፈራል። እንዲያውም የመገፋት መንፈስ አድሮባቸው ከእነርሱ ጋር ያለህ ግንኙነትም አደጋ ውስጥ ሊገባ ይችላል።"

"ዛሬ በጣም የተከበሩ እና ብዙ ሺዎች የበላይ ጠባቂ በመሆናቸው ደስተኛ የሆኑ መጋቢዎች አሉኝ። ግን እነኚህን መጋቢዎች ቤተ ክርስቲያን እንዲጀምሩ ከእኔ አርቄ ስልካቸው፣ አብዛኛውን ጊዜ አዝነውና የመገፋት ስሜት ተሰምቷቸዋል። ማማከርና ለእነርሱ ያለኝን ፍቅር በተደጋጋሚ መግለጽ ነበረብኝ።" በማለት አብራራሁለት።

ጓደኛዬ ምርጦቹን እንዲልክ በተደጋጋሚ አበረታታሁት። ደግሜም እንዲህ ስል አብራራሁለት፣ "በምትሞተው ዘር ልምምድ ውስጥ ካላለፉ፣ በፍጹም ፍሬ ሊያፈሩ አይችሉም። በዙሪያህ በመፈንጨት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉ ሥራዎች ራሳቸውን ይጠምዳሉ፣ እውነታው ግን ምንም ፍሬ አያፈሩም።"

## አንድን የወንጌል መልእክተኛ ቤተ ክርስቲያን ተካይ ቤተ ክርስቲያን እንዲተክል ስትልከው የሚያልፍባቸው ሂደቶች ምንድር ናቸው?

### 1. የመውደቅ ሂደት

የመውደቅ ሂደት የሚያሳየው በእግዚአብሔር ሰው ሕይወት ውስጥ በሕዝብ ዘንድ ታዋቂ የማይሆንበት እና የተሰወረ ሰው የሚሆንበትን ጊዜ ነው። በተጨማሪም የመገፋት፣ በጎ ያልሆነ ምላሽ፣ ተቀባይነት

ያለማግኘት፣ መካድ እና ውግዘትን የሚያይበት የሕይወት ጊዜ መሆኑን ያሳያል። ቤተ ክርስቲያን ተካዮች እና የወንጌል መልእክተኞች በእነኚህ ልምምዶች ውስጥ ብዙ ጊዜ ያልፋሉ። አትዘን፣ መገለል፣ መገፋት እና መለየት የእውነተኛ አገልግሎት አካሎች ናቸው።

መጥምቁ ዮሐንስን በተመለከተ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ለእስራኤል እስኪገለጥ ድረስ በምድረ በዳ ተሰውሮ እንደነበር ይናገራል። እያንዳንዱ አገልጋይ እግዚአብሔር ለሰውረው የሚፈልግበት ጊዜ እንዳለ ሊገነዘብ ይገባዋል። ያለ ጊዜው መገለጥ ወደ ጥፋት እንደሚያመራ አውቀህ ለመገለጥ አትቸኩል።

ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱ ለሕዝብ ከመገለጡ በፊት ለሠላሳ ዓመታት ተሰውሮ ነበር። በአገልግሎት ውስጥ ብቅ ማለቱ ዘሩ ለሠላሳ ዓመት በመሬት ውስጥ እንደነበር ሳላወቁ አስደነቃቸው።

ሙሴ ይህን ወደ ምድር መውደቅ አልፎበታል። ለመጀመሪያ ጊዜ ወንድሞቹን ለማገልገል ሲሞክር ፈጽሞ አገለሉት። አርባ ዓመት ሙሉ በምድረ በዳ አሳለፈ። ከብዙ የመገፋት እና የመገለል ዓመታት በኋላ፣ ለአገልግሎት ብቁ ሆነ።

ዮሴፍም እንዲሁ ወደ ምድር መውደቅን አልፎበታል። ራእዮቹና ሕልሞቹ ፈጽመው ተጥለዋል። ከዚያም እርሱ ራሱ ፈጽሞ ተገፍቶና ተወግዶ ነበር። ራሱን በባርነት ሲሠራ እና በኋላም በግብፅ እስር ቤት አግኝቶታል። ለብዙ ዓመታት ከወንድሞቹ ከተለየ በኋላ በመጨረሻ ለታላቅ አገልግሎት ዝግጁ ሆነ።

**እነኚህ በምድር ላይ የመውደቅ ሂደት ጥቂት ምሳሌዎች ናቸው። እውነቱን ነው የምልህ፣ የትኛውም እውነተኛ አገልጋይ ሳይገፋ ተቀባይነትን አያገኝም።**



## እኔም አልፌበታለሁ

እኔም በዚህ በምድር ላይ የመውደቅ ሂደት ውስጥ አልፌአለሁ። አገልግሎት ለመጀመር ስወጣ በእኔ ዘመን በነበሩ አገልጋዮች ፈጽሞ ተገፍቼ ነበር። ጥሩ ግንኙነት የነበረኝ አንዱ አገልጋይ ከዚህ በኋላ አላገለግላችሁም አለኝ። ለምን ብዬ ስጠይቀው፣ "ከዚህ በኋላ በእሾህ ላይ አልዘራም" አለኝ።

እርሱና ሌሎች መጋቢዎችም በእግዚአብሔር እንዳልተጠራሁና ቤተ ክርስቲያን መጀመር እንደሌለብኝ ተናገሩ። በትምህርቱ ላይ ማተኮር ያለበት የሕክምና ተማሪ መሆን እንዳለብኝ ተሰማቸው። ለረዳቱም ከእኔ ጋር ግንኙነት እንዳያደርግና በእግዚአብሔር ካልተጠራ ሰው ጋር መቆየት አደገኛ እንደሆነ ነገሩት።

ጥሩ ግንኙነት ለነበረኝ አንድ ሌላ አገልጋይም፣ ቤተ ክርስቲያን እንደ ጀመርኩ ነገርሁት። ወዲያው ተግሣጼን ተቀበልሁና የትኛው መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተምረህ ነው ተብዬ ተጠየቅሁ።

ተስፋ በመቁረጥ 'ጭራዬን እግሮቼ መካከል' አድርጌ ተመለስሁ። መገፋትን አጉልቶ ለማሳየት፣ ይህ መጋቢ የእኛ ቤተ ክርስቲያን በሚሰበሰብበት ቦታ ትልቅ ስብሰባ ለማካሄድ ወሰነ። ትልቅ ዝግጅት በማዘጋጀት በብሔራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያካሄደውን ፕሮግራም ኃይለኛ ቪዲዮ አሳየ። አቀራረቡ አይቼው በማላውቀው ሁኔታ የዚያን ሰው አገልግሎት የሚያሳይ ነበር። ከዚህ ትእይንት በኃላ የእኛ ቤተ ክርስቲያን የሽባና ድንክ ዳክዬዎች ስብስብ መሰለች። ከዚህ በኋላ ወደዚያ አገልግሎት እንድገባ ኃይለኛ ግብዣ ተደረገልኝ።

ከሄዱ በኋላ፣ ራሴን እንዲህ ስል ጠየቅሁ፣ "እንደዚህ ዓይነት ኃይለኛና የታወቀ አገልግሎት ከተማ ውስጥ እያለ ማን ወደ እኛ ሊመጣ ይችላል?" ከፕሮግራሙ በኋላ፣ ሞራላችን ተነክቶ ተስፋ ቆረጥን።

የአገልግሎትን ሥራ ለመፈጸም እየሞከርን በመታገል ላይ የነበርን የተማሪዎች ስብስብ መሆናችን ግልጽ ነው።

ከእነኚህ የተደላደሉ ቤተ ክርስቲያናት የአንዷ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ መጋቢ ማግኘቴንም አስታውሳለሁ። የተገናኘነውም በዩኒቨርስቲ ውስጥ በተካሄደ ሠርግ ላይ ነበር።

ሰላም ልለው ወደ እርሱ ስሄድ፣ "ኦ እንደምነህ ዳግ" አለኝ ከዚያም ትንፋሹን ሳብ አድርጎ ተመለከተኝና፣ "መጋቢ!" አለኝ።

ፊቱ እንደቆምሁ፣ መጋቢ ብሎ የጠራኝ እያሳገጠብኝ እንደሆነ ተሰማኝ።

"ጌታው ለምን ታሾፍብኛለህ?" "መጋቢ መሆኔን ሳታምንበት ለምን 'መጋቢ' ብለህ ትጠራኛለህ" ብዬ ልጠይቀው ፈለግሁ።

እንዴት ይህ ነገር ከአፌ ሳይወጣ እንደቀረ አላውቅም። ውድ ወዳጄ፣ እውነቴን ነው የምልህ፣ በዚያ የአገልግሎቴ ዘመን የተሰማኝ ነገር መገፋትና ማስፈራራት ነበር።

ፍጹም በሆነ መገፋት ውስጥ አልፌ ከማውቃቸው ብዙ አገልጋዮች ተለይቼ አገልግሎቴን ቀጠልኩ። ከዚያም እግዚአብሔር በትርፍ ጊዜ አገልጋዮችን በመጠቀም እንዳገለግል አስተማረኝ። አየህ፣ በዚያ ዘመን የነበሩ አብዛኞቹ አገልግሎቶች የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችን የሚጠቀሙ ነበሩ።

ተቀባይነት ስታጣና ተፈላጊ ሳትሆን ስትቀር አትጨነቅ። ማንም ሳይጋብዝህ ቢቀር አትበሳጭም። 'የምትታይበት' ቀን ይመጣል! ዛሬ፣ በመጀመሪያ ይንቁኝ በነበሩ አንዳንድ ታላቅ መጋቢዎች ተቀባይነት ያለኝ እና እንዲያውም የተከበርሁ ሆኛለሁ።

ምናልባትም እኔን ከመቀበል ሌላ ምርጫ ላይኖራቸው ይችል ይሆናል። የሆነ ሆኖ፣ ባይፈልጉኝም ይኸው አለሁ።



> ሕፃኑም አደገ በመንፈስም ጠነከረ፣ በእስራኤልም እስከታየበት ቀን ድረስ በምድረ በዳ ኖረ።
>
> ሉቃስ 1:80

## 2. መሞት

ዘር በምድር ላይ ሲወድቅ፣ ይበታተንና ይፈረካከሳል። ባሕሪውና ገጽታው ፈጽሞ ይለወጣል። እግዚአብሔር ሠርቶህ ሲጨርስ፣ ገጽታህ ይቀየራል። ባሕሪህ ፈጽሞ ይለወጣል። የመሞቱ ሂደት እንዲቀጥል ፍቀድ። ዘር ካልሞተ፣ ብቻውን ይቀራል። እነኚህ ብቃቶች እንዲዳብሩ ካልተደረገ፣ አገልግሎትህ አይዳብርም።

### i. ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነትን ማዳበር

በዚህ የመነጠል ጊዜ ውስጥ፣ ብዙ መንፈሳዊ ባሕሪያት በእግዚአብሔር ሰው ውስጥ ይወለዳሉ። ሰዎች ሲገፉህ ከምትማራቸው ነገሮች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት ነው። እውነተኛ የሆነ አገልጋይ ሁሉ ብርታቱን በቀጥታ ከጌታ ያገኛል፦ አየህ፣ የዚያን ቀን ብዙዎች ይመጡና፣ 'በስምህ አጋንንት አውጥቻለሁ፣ በስምህም ታላላቅ ነገሮችን አድርጌአለሁ'፣ይላሉ። ጌታ ግን እንዲህ ይላል፣ 'ፈጽሞ አላውቅህም'። ይህ ማለት እያንዳንዱ አገልጋይ ከጌታ ጋር ስላለው ግንኙነት እርግጠኛ መሆን አለበት ማለት ነው። መገፋት የአግድሞሽ(ከሰው) ግንኙነትን ያቆምና ወደ ላይ (ከእግዚአብሔር) ጋር ያለህ ግንኙነት እንዲዳብር ያደርጋል።

### ii. የትሕትና መዳበር

በሰው መገፋት ትሕትናን እንድታዳብር ያደርጋል። ትሕትና አገልጋይ ሊለብሰው የሚችለው ከፍተኛው መጎናጸፊያ ነው። አንድ አገልጋይ ይበልጥ ትሑት በሆነ ቁጥር፣ በጌታ ፊት በይበልጥ መቆሚያ ይኖረዋል! በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ በጣም የተለመደ ሽንገላ ቢኖር ትልቅ

ቤተ ክርስቲያን እለሀ ማለት፣ በጌታ ፊት ያለህ ቦታ ትልቅ ይሆናል ብሎ ማሰብ ነው። ጉዳዩ ግን ያ አይደለም፦ ጌታ ኢየሱስ ታላቅ መጋቢ የሚሆነው ከሁላችንም ይልቅ ትሑት የሆነና እንደ ልጅ የሆነው እንደሆነ በግልጽ አስቀምጧል።

> እንዲህ አለ፦ እውነት እላችኋለሁ ካልተመለሳችሁ (ካልተለወጣችሁ)
> እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም።
>
> ማቴዎስ 18፡3

የመጥምቁ ዮሐንስ ትሕትና ማስረጃ ነው። የኢየሱስን ጫማ ማሰሪያ እንኳ ሊፈታ እንደማይገባው ግልጽ አደረገ። እርሱ ሊያንስ ኢየሱስም ሊልቅ እንደሚገባ ስለ ጌታ ገለጸ። ዛሬ ምን ያህል መጋቢዎች ሌሎች እንዲልቁ እነርሱ ግን ሊያንሱ ይፈልጋሉ?

> እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል
>
> ዮሐንስ 3፡30

የኢየሱስ ትሑትነት ግልጽ ነበር። ኢየሱስ ራሱን ዝቅ አድርጎ እስከ መስቀል ሞት እንኳ ታዘዘ።

ሙሴ በራስ መተማመኑን ሁሉ አጣ። መጽሐፍ ቅዱስ እንደርሱ ያለ ትሑት ሰው በምድር ላይ እንደሌለ ይናገራል። አርባ ዓመት ሙሉ ከሚፈለጉ አሥር ሰዎች ውስጥ አንዱ ሆነህ በምድረ በዳ ብታሳልፍ ትሑት የምትሆን አይመስልህም? ስለ ሙሴ ጥሪ ስታነብ፣ ሙሴ እንዴት በራስ መተማመኑ ዜሮ እንደገባ ታያለህ። ታላቅ ሰው ነበር ግን ለራሱ የነበረው አመለካከት በእውነት በጣም ዝቅ ያለ ነበር። ሙሴ ስለ ራሱ ያለውን ግምት ተመልከት።

## የሙሴ አሥሩ አንድ ቅሬታዎች

1. ሙሴም እግዚአብሔርን 'እኔ ማነኝ'፣ አለ (ዘጸአት 3፡11)
2. ሙሴም እግዚአብሔርን .... 'ምን እላቸዋለሁ?' (ዘጸአት 3፡13)



3. ሙሴም መለሰ .......... 'አያምኑኝም ...' (ዘጸአት 4፡1)
4. ሙሴም እግዚአብሔርን ... 'ከቶ እንደበተ ርቱዕ ሰው አይደለሁም፣ ... እኔ ኮልታፋና ንግግር የማልችል ሰው ነኝ ' አለው (ዘጸአት 4፡10) (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)
5. እርሱም፦ 'ጌታ ሆይ፣ በምትልከው ሰው እጅ ትልክ ዘንድ እለምንሃለሁ' አለ። (ዘጸአት 4፡13)
6. ሙሴም...፣ '... ስለ ምንስ ላክኸኝ?' አለ። (ዘጸአት 5፡22)
7. ሙሴም እንዲህ ብሎ ተናገረ ' ... የእስራኤል ልጆች አልሰሙኝም።' (ዘጸአት 6፡12)
8. ሙሴም እግዚአብሔርን እንዲህ አለው፣ ' ... እነሆ እኔ ከንፈረ ቆላፋ ነኝ' (ዘጸአት 6፡30)
9. ከዚያም ሙሴ፣ '... በድንጋይ ሲወግሩኝ ተዘጋጅተዋል' ብሎ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ (ዘጸአት 6፡30)
10. ሙሴም እግዚአብሔርን እንዲህ ሲል ጠየቀው፣ 'እንዲህ ያለውን መከራ በባሪያህ ላይ ለምን አመጣህ?' (ዘኁልቁ 11፡11) (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)
11. ሙሴ ግን እንዲህ አለ፣ እነሆ እኔ በስድስት መቶ ሺህ እግረኛ መካከል እገኛለሁ (ዘኁልቁ 11፡21)

ዮሴፍ ለተወሰኑ ዓመታት እስረኛ ሆኖ ካሳለፈ በኋላ ወንድሞቹን ሲያይ በቀልን አላሰበም። በዚህ ሁሉ ውስጥ እግዚአብሔር ነገርን ሁሉ ለበጎ እንዳደረገ ተገነዘበ።

ዮሴፍ በእግዚአብሔር ነገር እጅግ ስለበሰለ ወንድሞቹ ምንም ክፉ ነገር እንዳላደረጉበት ሆኖ ተሰማው። እንዲያውም እግዚአብሔር ወንድሞቹን እንደተጠቀመባቸው ነበር የተሰማው።

## እኔም አልፌበታለሁ

ባላፍሁበት ነገር ሁሉ ካለፍሁ በኋላ፣ በአንድ ወቅት የገፉኝን ሰዎችን ማፍቀርና ማድነቅ ቻልሁ። እግዚአብሔር እኔን በአገልግሎት ውስጥ ለማሠልጠን እንደተጠቀመባቸው ይሰማኛል። በማናቸውም ላይ ቂም አልያዝሁም፣ ለአገልግሎታቸውም የምሰጠው ዋጋ ትልቅ ነው። ያሳለፍኋቸው መራር ነገሮች እንኳ ለበጎ ሆነውልኛል።

## 3. ብዙ ፍሬ ማፍራት

ፍሬ ማፍራት በጣም መንፈሳዊ ነገር ነው። ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ካለህ፣ ብዙ ፍሬ እንዳፈራህና እግዚአብሔርን ደስ እንደምታሰኝ ያስባሉ።

ይሁን እንጂ ጌታ ኢየሱስ የመጀመሪያውን ስብከቱን ከመስበኩ በፊት እንኳ አባቱን ደስ እንዳሰኘ ማየት ትችላለህ።

> እነሆም፣ ድምፅ ከሰማያት መጥቶ፡- በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጅ ይህ ነው አለ።
>
> ማቴዎስ 3፡17

በሰማይ ያለ አባትህ፣ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጅ ይህ ነው።" እንዲልህ ቤተ ክርስቲያን እንዲኖርህ አያስፈልግም። መጋቢ እንኳ መሆን አያስፈልግህም መጽሐፍ መጻፍ አያስፈልግህም፣ ዓለም እንዲሰማህ ስብከት መስበክ የለብህም፣ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጅ ይህ ነው።"

"በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጅ ይህ ነው።" የሚሉ ቃላትን ለመስማት ታዋቂ ሰው መሆን አያስፈልግህም። ይህ ሲሆን ኢየሱስ ታዋቂ አልነበረም። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የሚያሳየን



እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት የሚለካው በሥራችን እንዳልሆነ ነው። በእርግጥ ፍሬዎቻችን በጌታ የተሰጡን ስጦታዎች ናቸው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ባፈራው እጅግ ሰፊ ፍሬ ተገርመህ ታውቃለህ? በሦስት ዓመት አገልግሎቱ ምክንያት እንዴት በሺህዎች የሚቆጠሩ ቤተ ክርስቲያናት ተተከሉ ብለህ ተገርመህ ታውቃለህ? ሁለት ሺ ዓመታት ቢያልፉም ከቀድሞው ይልቅ እያፈራ ነው። እንዲህ ብዙ ፍሬ ሊያፈራ የቻለው ምን ቢያደርግ ነው?

ስድስት ነገሮች ነው ያደረገው፡ የሦስት ዓመት ስብከት፣ ማስተማር እና መፈወስ፣ የትሕትና ሕይወት መኖር፣ መታዘዝ እና በመስቀል ላይ መሥዋዕት መሆን። ከእነኚህ ውስጥ የጎላው የደህንነታችንን በር የከፈተው የመስቀል ላይ መሥዋዕትነት ነው። ለጌታ መታዘዝህና መሥዋዕትነት መክፈልህ ለብዙ ቤተ ክርስቲያናት መነሣት ምክንያት ይሆናል።

## መሥዋዕት አቅርብ፣ መሥዋዕትም ሁን

ዋና መጋቢ ከሆንህ፣ ያሉህን ምርጦችህን ለመላክ አትፍራ። እግዚአብሔር አንድ ልጁን ሰጥቶ ዛሬ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ልጆች አሉት። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እንድትተክል ከጠራህ ለመሞት አትፍራ። ካልሞትህ በቀር፣ በፍጹም ብዙ ፍሬ ልታፈራ አትችልም።

ለጌታ የመሠዋት እና መሥዋዕት የመሆን ጊዜ ነው። ምርጥ መሪዎችህንና ሠራተኞችህን በዓለም መከር ላይ አውል። ራስህንም ለጌታ ለማዋል ፍቀድ።

ይህ የዴቪድ ሊቪንግስተን ፍልስፍና ነበር። ራሱን፣ ሳልዳኑት ነገዶች እና ሊገኙና በወንጌል ሊደረሱ ለሚችሉ ሕዝቦች፣ ሊሰጥ ወሰነ። ከመሞቱ በፊት የተደረገለትን ቃለ ምልልስ እጠቅሳለሁ።

## ዴቪድ ሊቪንግስተን፡ መሥዋዕት ማቅረብ እና መሠዋት!

*በዐሥራ ሁለት ዓመቱ፣ ለመንፈሳዊ ሕይወቱ ደንንነት ጉጉትን አሳየ:: በሃያ ዓመቱ ተለወጠ:: ይህ ከክርስቲያን ቤተሰብ ከመሆን ወደ ቤተ ክርስቲያን አባልነት የመሸጋገሪያ ዓለት ነበር::*

*አብሯቸው ሕብረት የሚያደርጋቸው ሰዎችም በሀሚልተን ቤተ ክርስቲያን የሚያመልኩ ነበሩ:: ሁለት ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያንን የእምነት አቋም አስተማሩት:: ለአምስት ወራት አንዱ ሽማግሌ እንዲያስተምረውና እንዲጸልይለት ብላንቲይር ከሚገኘው ቤቱ ሐሚልተን ወደምትገኘው ትንሿ ቤተ ክርስቲያኑ ያለማቋረጥ ተመላለሰ:: ከዚህም በኋላ ሙሉ በሙሉ አባል እንዲሆን ተደረገ::*

*ኪዚህ በኋላ ነበር ለክርስቶስ አገልግሎት በወንጌል መልእክተኝነት ራሱን አሳልፎ ለመስጠት የወሰነው::*

*በሕክምና እና በሥነ- መለኮት ከተመረቀ በኋላ፣ ለሎንደን ሚሽነሪ ሶሳይቲ አመለከተ:: ሊቃለ - መጠይቅ መምጣት ትችል ይሆን? ተብሎ ቢጠየቅም ገንዘብ አልነበረውም:: ሁለት ጓደኞቹ ረዱት:: አስፈላጊው የሎንደን ትምህርት ቤት ግዳጅ አለቀና፣ ሕይወትን ሊጋፈጥ ዝግጁ ሆነ::*

*ምርጫው ቻይና ነበር:- ግን የኦፒየም ጦርነት በሩን ዘጋበት፣ ልቡ ወደ አፍሪካ ዞረ፣ ወደዚያ አሕጉር በመርከብ ተጉዞ በ1849 እ.ኤ.አ ኬፕ ታውን ደረሰ::*

*በመርከብ ሲጓዝ ምን ይመስል ነበር? ዘለግ ያለ፣ አቋሙ ቀጠን ያለ፣ ሕይወትን ለመጋፈጥ ቁርጠኝነት የሚታይበት ገጽታ የሚታይበት ሰው ነበር::*

*እንደ ምክንያት አድርጎ ያቀረበው:- "በመጀመሪያ የወንጌል ቅንአት በልቤ እየሰፋ እንደመጣ ሲሰማኝ፣ ደስ የሚያሰኘኝ ጥያቄ እየሆነ መጣ:- በቀሪው ዘመኔ እንዴት ብዬ ነው ሌሎች ወገኖቼን ወደዚህ ደስታና ሰላም እንዲገቡ በማድረግ የማሳልፈው?"*

*ዓመታቶቼን እንዴት ነው የማሳልፈው? . . ."መሠዋትና መሥዋዕት መሆን"*

*ለወንጌል መልእክተኝነት ያለው ፍጹም ሐሳብ በዘመናት መካከል የማይለወጥ ነበር::*

*ሊቪንግስተን መስበክና ማስተማር ብቻ ሳይሆን ለታመሙትም ሐኪም ነበር:: ከእነኚህ አፍሪካዊያን ጋር ወዳጅነት የመፍጠር ተሰጥኦም ነበረው:: "ማፍቀር መፈቀርን ያመጣል" መመሪያው ነበር:: እጆቹ በፍጹም ሥራ አይፈቱም ነበር:- ግንበኛ፣ አናጢ፣ ጠራቢ እና የሚኖርበት አካባቢ የማኅበራዊ ኢኮኖሚ ዳይሬክተር በመሆን ዘመኑን ኃይለኛ ተግባራትን በመፈጸም አሳለፈ::*



*እንደ ዴቪድ ሊቪንግስተን ያሉ ታላላቅ ሰዎች መሥዋዕትነት በአፍሪካ ውስጥ ታላቅ የሆነ የቤተ ክርስቲያን መስፋፋትን አመጣ:: በእውነት መሠረቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ከተጣለው የመሥዋዕትነት መንገድ በቀር ሌላ መንገድ የለም:: እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ዘለቄታ የሚኖራት በመስዋዕትነት ብቻ ነው::*

***ከዚህም ሁሉ በላይ፣ ልጄ ሆይ፣ ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም!***

*ምዕራፍ 18*

# መታዘዝ
# እና
# ቤተ ክርስቲያን መትከል

**ሳሙኤልም፡- በውኑ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው እግዚአብሔር በሚቃጠልና በሚታረድ መሥዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ፣ መታዘዝ ከመሥዋዕት፣ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል።**

**1ኛ ሳሙኤል 15፡22**

ብዙውን ጊዜ መሥዋዕት የሚሆን ሰው ከሚታዘዝ እንደሚበልጥ አድርገን እናስባለን። መሥዋዕትነት የሚለው ቃል፣ አስፈሪ የሆነ የሥቃይና የመጥፋትን ሐሳብ ያመጣብናል። መታዘዝ ቀላልና ብዙ የማይጠይቅ ምርጫ ይመስላል። በእርግጥ፣ እንደ ሰው የምናደርገው ምርመራ በማንኛውም ጊዜ መሥዋዕትነትን ከመታዘዝ በላይ ያደርገዋል።

አሁንም፣ የእግዚአብሔር መንገድ ከእኛ መንገድ የተለየ ነው፣ ሐሳቡም ከእኛ ሐሳብ የተለየ ነው። መታዘዝ ከመሥዋዕትነት እንደሚበልጥ ግልጽ አድርጎልናል። "የተሻለ የሚለው ቃል የበለጠ፣ የሚመረጥ፣ የተሻሻለ፣ የላቀ፣ የጨመረ፣ ይበልጥ ተቀባይነት ያለው፣ ይበልጥ የሚመረጥ፣ የተሻለ ብቃት፣ ያደገ፣ እና ይበልጥ የሚፈለግ ማለት ነው!" ስለዚህ ጥቅስ መታዘዝ ከመሥዋዕትነት ይልቅ 'የሚበልጥ፣



የሚመረጥ፣ የላቀ፣ ይበልጥ ተቀባይነት ያለው፣ ይበልጥ ተመራጭነት ያለው እና ይበልጥ ተፈላጊነት አለው' ማለት ነው።

ለምንድር ነው መታዘዝ ከመሥዋዕትነት የሚመረጠው? አብዛኛውን ጊዜ መሥዋዕትነት ስንከፍል ምን እየሠራን እና ለምን መሥዋዕትነት እየከፈልን መሆኑን እናውቃለን። መከራ እንደምንቀበል እና መከራ የምንቀበልበትን ምክንያት እናውቃለን። ለምንድር ነው መታዘዝ በእግዚአብሔር ፊት ይበልጥ ተፈላጊ፣ የሚመረጥ እና ይበልጥ ተቀባይነት ያለው?

የሚከተሉት ምክንያቶች መታዘዝ ከመሥዋዕትነት ጋር ሲነጻጸር ለምን እንደሚበልጥ ይገልጻሉ።

## መታዘዝ ከመሥዋዕትነት ለምን ይሻላል(ይበልጣል)

### 1. ሙሉ መረዳት ሳይኖር መታዘዝ ከመሥዋዕትነት ይበልጣል

በሕይወቴ እና በአገልግሎቴ ውስጥ ትልቁ በረከት የመጣው ለእግዚአብሔር ከከፈልሁት መሥዋዕትነት ይልቅ በመታዘዝ ነው። አብዛኛውን ጊዜ፣ የምታደርገውን ነገር እንደምታ መገንዘብ አስቸጋሪ ነው። አሁን ይህን መጽሐፍ ስጽፍ፣ ጌታ እንዳደርግ የጠየቀኝ እና ያልተረዳኋቸው ነገሮች አሉ።

የማንረዳበት ምክንያት በጌታ ካለን የእድገት ደረጃ ወይም የብስለት ደረጃ የተነሣ ነው። ጌታ አድርጉ ያለንን ማድረግ እስካልጀመርን ድረስ በምንም ዓይነት ሙሉ በሙሉ ልንረዳው እንደማንችል አምናለሁ። ይህን ጥቅስ ልብ በል። የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምትረዳው ስትፈጽመው እንደሆነ ያሳይሃል።

> ማንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ቢፈልግ፣ የእኔ ትምህርት ከእግዚአብሔር ወይም ከራሴ የመጣ መሆኑን ለይቶ ያውቃል
>
> ዮሐንስ 7፡17
>
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

የትርፍ ጊዜ መጋቢ በነበርሁበት ጊዜ የሙሉ ጊዜ አገልግሎት ያለውን ተጽዕኖ እንዴት ልረዳ ቻልሁ? ብዙ የትርፍ ጊዜ አገልጋዮች የሙሉ ጊዜ አገልግሎት ምን እንደሆነ የሚረዱት ይመስላቸዋል፡፡ ግን ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት ተገቢውን ዋጋ እንደማይሰጡት አውቃለሁ፡፡ ብዙ የትርፍ ጊዜ አገልጋዮች ከማንኛውም ሰው እኩል እግዚአብሔርን እያገለገሉ እንደሆነ አድርገው ያስባሉ፡፡ የሙሉ ጊዜ አገልግሎትን አስፈላጊነት የተረዳሁት እግዚአብሔርን በመታዘዝ ብቻ ነው፡፡

## 2. በተፈጥሮ የማደርገውን ነገር መታዘዝ፣ ከመሥዋዕትነት ይበልጣል

ጌታ ወደ ፊውስ አገልግሎት ሲመራኝ፣ በአገልግሎቱ ላይ የሚኖረውን ውጤት አልተረዳሁም ነበር፡፡ እስከዚያን ጊዜ ድረስ፣ የምሠራው ማስተማርና መስበክ ነበር፡፡ እኔ በተፈጥሮዬ ነገሮችን አስልቼና አመዛዝኜ የምሠራ ሰው ነኝ፡፡ ለእኔ በመንፈስ መመራት ወይም መንፈሳዊ የሆኑ ነገሮችን ማገልገል የተለመደ አልነበረም፡፡ ይህን ማድረግ ለእኔ በጣም አስቸጋሪ ነገር ነበርና ይህን እንቅፋት እንዳልፍ ለረዱኝ ሰዎች ያለኝ ምስጋና የላቀ ነው፡፡ ዛሬ በአገልግሎቴ ውስጥ ብዙ ተአምራቶችን አይቼአለሁ፡፡ በዛሬው አገልግሎቴ ላይ ከፍተኛ ልዩነት ካመጡ ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው ለማለት እችላለሁ፡፡

> አባት ሆይ፣ ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ፡-
>
> ሉቃስ 22፡42



በተፈጥሮ በክፉ ሰዎች ለመገደል ራስን አሳልፎ መስጠት በጣም ያልተለመደ ነገር ነው፡፡

ለሰው ልጅ እጅግ አስፈሪ ከሆኑ ነገሮች አንዱ ልትሞት እንደሆነ ማወቅ ነው፡፡ በተያዙበት በሽታ እንደሚሞቱ ሲነገራቸው ወዲያው የሞቱ በሽተኞች ነበሩኝ፡፡ ብታስበው፣ አስፈሪ ልምምድ እንደሆነ ታውቃለህ፡፡

የደም ካንሰር (ሉኪሚያ) የነበረባት ሴት አስታውሳለሁ፡፡ ለሕክምና ስትመጣ የሆነ ትኩሳት ነገር መስሏት ነበር፡፡ ምንም እንኳ ገዳይ በሽታ ቢኖርባትም ጤናማ ትመስል ነበር፡፡ አንድ ማለዳ፣ ዶክተሮች ጉብኝት ሲያደርጉ፣ አንዱን ዶክተር የሥራ ባልደረባዬን መድኃኒቷን ከየት ማግኘት እንደምትችል ጠየቀችው፡፡ የሥራ ባልደረባዬም ወደ መንገዱ በመጠቆም፣ "አ፣ እነኚህን የካንሰር መድኃኒቶች ከመንገዱ ማዶ በሚገኘው መድኃኒት ቤት ማግኘት ትችያለሽ"፣ አላት፡፡ ሴትየዋ ጸጥ አለች! ደነገጠች! እስከዚህ ሰዓት ድረስ፣ ካንሰር ወይም እንደዚህ የለ ሕመም እንዳለባት አልተነገራትም ነበር፡፡ ይህች ሴት በጣም ከመፍራቷ የተነሣ ሁኔታዋ በከፍተኛ ደረጃ እየባሰ ሄደ፡፡ ይህን ስል በጣም አዝናለሁ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ፣ ራሷን ስታ ሞተች፡፡

ወደ ሞት መቃረብን ማወቅ በማንኛውም ሰው በጣም አስፈሪ ከሆኑ ሥቃዮች አንዱ ነው፡፡ ከምሕረቱ የተነሣ፣ እጅግ አልፎ አልፎ ካልሆነ በቀር እግዚአብሔር የምንወሰድበትን ቀን አያሳየንም፡፡

በፊኛ ችግር ምክንያት ሊሞት የተቃረበና ዓይኑ ደም የለበሰ የሠላሣ ዓመት ወጣት በውስጥ ደዌ ክፍል ተኝቶ ሁልጊዜ ትዝ ይለኛል፡፡ እጅግ አደገኛ በሆነ ሁኔታ ችግር እንዳለበት አውቋል፡፡ አንድ ቀን ማለዳ ምርመራ ሳደርግለት፣ እጄን ጎተት አድርጎ፣ "ዶክተር፣ እባክህ እርዳኝ፡፡ ወደ ጀርመን መሄድ እፈልጋለሁ፡፡ በዚያ የሕክምና እርዳታ እንዳገኝ

የሚረዳኝ ወንድም አለኝ" አለኝ። የሕክምና ተማሪ በመሆኔና ምን ማድረግ እንደሚገባኝ ባለማወቁ ፈራሁ።

ጎንበስ ብዬ ስመለከት የሽንት ማጠራቀሚያው ላስቲክ በደም ተሞልቶ አየሁና ሊያድነው የሚችል እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ አወቅሁ። በዚያ ሰው ዓይን ውስጥ የነበረውን ፍርሃት ሁልጊዜ አስታውሳለሁ። የፍርሃትና የልመና ድምፁ ሁልጊዜ ትዝ ይለኛል። "ዶክተር፣ እባክህ እርዳኝ።"

የእኔ ኢየሱስ እንዴት ብሎ አሰቃቂ ሞቱን ሳስብ፣ ይደንቀኛል። ኢየሱስ እንዴት እግዚአብሔር ጽዋውን ከእርሱ እንዲወስድ እንደ ጸለየ ሳስብ ለአባቱ ያለውን ታዛዥነት አደነቃለሁ።

ውድ ወዳጄ፣ ወደ ሞትህ መሄድ የተለመደ ነገር አይደለም። ራስህን የሚጎዳ እና የሚያጠፋ ነገር ማድረግ ቀላል ነገር አይደለም። መታዘዝ ከመስዋዕትነት ይሻላል!

ከተፈጥሮአዊው አዕምሮህ ወይም አስተሳሰብህ ጋር የማይሄዱ ብዙ የእግዚአብሔር ትእዛዛት አሉ። ጊዜው የመታዘዝ ነው። እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ውስጥ እየኖሩ ተጨማሪ መባ የሚሰጡ ሰዎች አሉ። እነኚህ ተጨማሪ መሥዋዕቶች የሚሰጡት ያለመታዘዝ ሕይወታቸውን ለማካካስ ነው። እስቲ እሁድ እሁድ ልብ ብለህ ተመልከት፣ ብዙ የማይታዘዙ ክርስቲያኖች ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ለጌታ ሲሰጡ ትመለከታለህ፤ ይህንን የሚያደርጉት የእግዚአብሔርን ዐይኖች በእነኚህ መባዎች እንጨፍናለን ብሎ ተስፋ በማድረግ ነው። ምሕረት!

## 3. ከመሥዋዕትነት ይልቅ፣ የማትስማማባቸውን ትዕዛዞች መታዘዝ ይሻላል

አለመታዘዝ ብዙውን ጊዜ የሚገባብህ በተሰጠህ ትእዛዝ ሳትስማማ ስትቀር ነው። እግዚአብሔር ዐመፀኝነቱ እርግጥ የሆነን ሰው ይቅር በል



ሲለን፣ ለመስማማት ዝግጁ ሳንሆን እንችላለን። እየቆየ ሲሄድ፣ ይቅር ማለት ከበቀል እንደሚበልጥ ትደርስበታለህ። በደል በደረሰብህ ጊዜ ሁሉ፣ የበደለህን ሰው ማረም እንደሚገባህና ዋጋውን ልትከፍለው እንደሚገባህ የሚሰማህ ራስን በጣም የማጽደቅ ስሜት አለ። ይህን ስሜት ችላ ማለት ቀላል ነገር አይደለም!

ያሳዘኑኝን ሰዎች ይቅር በማለቴ ምክንያት ትልልቅ በረከቶች ወደ እኔ መጥተዋል። ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር አደራረግ ጋር መስማማት ቀላል ነገር አይደለም።

> ከእነዚህም ነገሮች በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው፤ እንዲህም አለው፦ አብርሃም ሆይ። አብርሃምም፦ እነሆ፣ አለሁ አለ። የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ፤ እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው አለ። አብርሃምም በማለዳ ተነሥቶ አህያውን ጫነ፤ ሁለቱንም ሎሌዎቹንና ልጁን ይስሐቅን ከእርሱ ጋር ወሰደ፤ እንጨትንም ለመሥዋዕት ሰነጠቀ፤ ተነሥቶም እግዚብሔር ወዳለው ቦታ ሄደ።
>
> ዘፍጥረት 22፡1-3

እርግጠኛ ነኝ አብርሃም አንድ ልጁን በመግደል ሐሳብ አልተስማማም ግን እግዚአብሔር አድርግ ያለውን ነገር አደረገ።

## 4. ከመሥዋዕት ይልቅ፣ የሚያዋርድ ትእዛዝን መታዘዝ ይሻላል

ብዙዎቹ የእግዚአብሔር ትእዛዞች ዝቅ ያደርጉናል። የእግዚአብሔር ትእዛዝ እንደኛው ባህሪ ዝቅ የሚያደርግ ነው ማለት ይቻላል። ብዙውን ጊዜ በሰዎች እና በራስህ ዓይን ፊት ሞኝ ያስመስልሃል።

እግዚአብሔር የሙሉ ጊዜ አገልጋይ እንድሆን ሲመራኝ፣ በሌሎች ዶክተሮች ፊት ሞኝ መስዬ ታየሁ። መባ ስሰበስብና ገንዘብ ሳሰባስብ፣ በራሴና በብዙ ሰዎች ዓይን ሞኝ እመስላለሁ።

እግዚአብሔር ወደ ሙሉ ጊዜ አገልግሎት ሲጠራኝ ለጌታ ታላቅ መሥዋዕትነቶችን ላደርግ አቀድሁ። ከምከፍተው ትልቅ ሆስፒታል ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ እሰጥሃለሁ፣ አልሁት። ይሁን እንጂ፣ ጌታ መሥዋዕቴን እንደማይፈልግ ነገረኝ፣ ይልቅ ለእርሱ እንድሠራ ፈለገ።

## የሚያካክስ የትርፍ ጊዜ መጋቢ

አንድ ቀን አንዱን የትርፍ ጊዜ መጋቢዬን ጠራሁና ከአክራ ጋና 272 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ወደምትገኘው ኩማሲ ወደምትባል ከተማ አብሮኝ እንዲጓዝ ጠየቅሁት።

"ትመጣለህ" ብዬ ጠየቅሁት

"ከአንተ ጋር መጓዝ ትልቅ እድል ነው"፣ አለና፣ "ከሥራ ሹልክ ብዬ ከአንተ ጋር እመጣለሁ" አለኝ።

እየነዳሁ ስንሄድና ስናወራ፣ አንድ ያስደነቀውን ነገር ነገርሁት።

"በጣም ጠንካራ ሠራተኛ ወጣት ነህ" አልሁት በመቀጠልም፦ "ሁልጊዜ ለጌታ ተጨማሪ ነገሮችን ትሠራለህ።" አየህ፣ ይህ ወጣት ያሕንፃ ዲዛይን ሠራተኛ(አርክቴክቸር) ነው፣ ከሥራው ሌላ፣ ያለ ማቋረጥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይሠራል።

እንዲህ አልኩት፦ "ሊፈጸም የሚገባውን ማንኛውንም ነገር ለመፈጸም ከተማ ውስጥ ትሯሯጣለህ። ካሉኝ በጣም መሥዋዕትነት ከሚከፍሉና የተሰጡ መጋቢዎቼ መካከል አንዱ ነህ።"

ታላቅነት ተሰምቶት ፈገግ አለ!

ቀጠልሁ፦ "ለቤተ ክርስቲያን ብዙ የሕንፃ ዲዛይን ሥራዎች ሠርተሃል ግን አንዲት ሳንቲም ጠይቀህ አታውቅም። ተጨማሪ የመጋቢነት ሥራ በሚኖርበት ጊዜ ሁሉ፣ አንተን ነው የምጠራው"።



እንዲህም ስል ገለጽሁለት፦ "ለዚያህ ነው አብረኸኝ እንድትሄድ የጠራሁህ። ለመሥሪያ ቤትህ ወዲያው ነግረህ መምጣት እንደምትችል አውቃለሁ።"

ከዚያም ያልታሰበ ቦንብ ጣልሁበት፣ "ግን ባለመታዘዝ ውስጥ ትገኛለህ!" ቀጥዬም፣ "እግዚአብሔርን አልታዘዝ ብለሃል።" ፈገግታው መጥፋት ጀመረ።

እንዲህ ብዬ ገለጽሁለት፣ "በጣም ንቁ፣ በጣም ቀናተኛ እና በጣም መሥዋዕት ከፋይ የሆንኸው እግዚአብሔርን አለመታዘዝህን ለማካካስ ነው። እግዚአብሔር ወደ ሙሉ ጊዜ አገልግሎት ጠርቶሃል አንተ ግን ሩጫ ላይ ነህ።"

"ደነገጠ።" "በፍጹም አስቤበት አላውቅም፣" አለ። "አለመታዘዙን ለማካካስ እየሞከርሁ እንደሆነ በፍጹም መጥቶልኝ አያውቅም።"

ከጥቂት ወራት በኋላ፣ ይህ ወጣት ሰው ሥራውን ትቶ ለሙሉ ጊዜ የአግልግሎት ጥሪው ታዘዘ። እግዚአብሔር ዓይኖችህን አብርቶ እርሱን ባለመታዘዝ ውስጥ ከሆንህ እና ለማካካስ እየሞከርህ ከሆነ ያሳይህ!

ኦ እንዴት አለመታዘዛችንን ማካካስ እንወዳለን! ራሳችንን በእግዚአብሔር ፊት ማዋረድ አንወድም። በማንም ፊት ሞኝ መምሰል አንፈልግም። የራሳችንን ነገር ለማድረግና አመቺ መሥዋዕትነት በማድረግ ለማካካስ እንሞክራለን።

> በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፤ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ።
>
> ፊልጵስዩስ 2:8

## 5. ከመሥዋዕትነት ያንተን ጥበብ የማይጠይቀውን ትእዛዝ መታዘዝ ይሻላል

> ወርቅ ወይም ብር ወይም ናስ በመቀነታችሁ፤ ወይም ለመንገድ ከረጢት ወይም ሁለት እጀ ጠባብ ወይም ጫማ ወይም በትር አታግኙ፤ ለሠራተኛ ምግቡ ይገባዋልና።
>
> ማቴዎስ 10:9-10

እንዴት ለራሴ ብርና ወርቅ ሳላከማች እኖራለሁ? ከጌታ ጋር መጓዝ የራስህን ምክንያት እና በጥበብህ መታመንን ወደ ጎን መተውን ይጠይቃል። ለእግዚአብሔር ለመሥራት የሚያስፈልገው እምነት ነው።

በውስጧ የሚቃጭሉ ሳንቲሞች የያዘች ትንሽ የመባ ቅርጫት ከወንበር ወደ ወንበር ስትዞር ስታይ፣ "በእንዲህ ሁኔታ በተሰበሰቡ ሳንቲሞች መኖር እችላለሁ?" ብለህ ትጠይቃለህ።

እግዚአብሔር የሙሉ ጊዜ መጋቢዎችን የሚያኖረው በዚህ ነው? ከዓመታት በፊት፣ አውሮፓ ውስጥ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ጎበኘሁ። አሜሪካዊው የወንጌል መልእክተኛ መጋቢ የዳበረ ጉባዔ አለው። ቢሮው ውስጥ እንደተቀመጥሁ፣ ስለ አገልግሎት የገንዘብ ሁኔታ መናገር ጀመርሁ።

በኩራት እንዲህ ስል ነገርኩት፣ "እኔ በመባ የምደገፍ መጋቢ አይደለሁም።" በመቀጠልም፣ "በዶክተርነት እየሠራሁ ሌላም የግል ሥራ አለኝ። የማንም ገንዘብ አያስፈልገኝም።"

በመገረም እየተመለከተኝ እንዲህ አለኝ፦ "በምታደርገው ነገር ውስጥ ጥበብህን ማየት እችላለሁ ግን የእግዚአብሔር ጥበብ ከአንተ ጥበብ ይበልጣል።"

ሲያብራራልኝም፣ "እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑን የሚገነባበት ዕቅድና ንድፍ አለው። የአንተ ዕቅድ እና ሐሳብ ከእርሱ ዕቅድ በፍጹም ሊበልጥ አይችልም።"

የእግዚአብሔር መንገድ ቀላል ነው! "ወንጌልን የሚሰብኩ በወንጌል ሊኖሩ ይገባቸዋል" (1ኛ ቆሮንቶስ 9:14)

እንዲህ አለኝ ፦ "ጉባዔህ የእግዚአብሔርን ሰው በመባረክ የሚቀበለውን በረከት እንዳያገኝ እየከለከልከው ነው።"



ራሴን ጻድቅ በማድረግ ፦ "እነኚህ መባዎች አያስፈልጉኝም" ብዬ ለራሴ አሰብሁ።

ይሁን እንጂ፣ ከዚያ ንግግር በኋላ ከእግዚአብሔር የበለጠ ጥበበኛ እንዳልሆንሁ ተገነዘብሁ።

እግዚአብሔር ከእኔ የበለጠ እንዴት ቤተ ክርስቲያኑን እንደሚገነባ ማወቅ አለብኝ።

ዛሬ፣ ወንጌል እሰብካለሁ በወንጌል እኖራለሁ። እግዚአብሔር መጋቢዎች እንዲኖሩበት ባዘጋጀው መንገድ በቅሕትና እኖራለሁ። ከማናቸውም የእግዚአብሔር ባሪያ አልበልጥም። በመነገድ እና ሌሎች ገንዘብ ማግኛ መንገዶችን በመፈለግ፣ ጊዜ ከመሠዋት፣ ገንዘብ ማምጣት ለሚችለው የቃሉና የጸሎት አገልግሎት ራሴን ሙሉ በሙሉ ሰጥቼአለሁ። ከመሥዋዕትነት ይልቅ መታዘዝ ይበልጣል።

## 6. አስቸኳይ ወይም አስፈላጊ የማይመስሉ ሥራዎችን ለመሥራት ታላቅ ታማኝነትና ትጋትን ይጠይቃል

እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

ማቴዎስ 28:19-20

ሳታቋርጡ ጸልዩ

1ኛ ተሰሎንቄ 5:17

ብዙ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች አስቸኳይ አይደሉም። አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች የማይስቡ እና የማያጓጉ ናቸው። እግዚአብሔር አስፈላጊ አድርጎ የሚያያቸውን ነገሮች ላይ ታማኝ መሆን ያስቸግራል።

ለምሳሌ ያህል፣ ሳያቋርጡ መጸለይ ልናደርጋቸው ከሚገቡን ነገሮች ውስጥ በጣም አስፈላጊው ነው። ግን የጸሎት ነገር ሲነሣ አስቸኳይነቱ አይታየንም።

በችግር ጊዜ፣ ባብዛኛው እምነት ሊኖርህ አይችልም። በችግር ውስጥ በምትሆንበት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ለመጮኽ እየፈለግህ ፍርሃትና ጭንቀት ልብህን ይይዛል። በእነኚያ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ፈጽሞ መጸለይ አይቻልም ለማለት ይቻላል። የዚያን ጊዜ መጸለይ እንዴት አስፈላጊ እንደነበር ትረዳለህ።

የእምነት ጽንሰ ሐሳቦች(Theories) ሁሉ ሊሠሩ በማይችሉበት ጨለማ ውስጥ ገብቼ አውቃለሁ። ኢየሱስ ከተያዘ በኋላ ለምን አልጸለየም ብለህ አስበህ ታውቃለህ? ምክንያቱም ችግሩ ከመምጣቱ በፊት ጸልዮ ስለጨረሰ ነው። ኢየሱስ የአልአዛርን መቃብር ጋር ሲደርስ እርሱን ከሞት ከማስነሣቱ በፊት እንዴት ጸሎት መጸለይ አላስፈለገውም ነበር። የጸለየበትንም ብቸኛ ምክንያት ሲያስረዳ በዙሪያው ያሉ አባት እንዳለው ያውቁ ዘንድ ነው። ወንጌልን መስበክ እና የጠፉትን መማረክ በጣም አስፈላጊ የሆነ ትእዛዝ ነው። ግን አብዛኛው ያንን ትእዛዝ ለመፈጸም አጣዳፊ መስሎ አይታይም። ግፊት አልተሰማህም ማለት ግን አስፈላጊ አይደለም ማለት አይደለም። ግፊት የትእዛዝን አስፈላጊነት ሁል ጊዜ አያሳይም። ግፊት በሌሰብን ሰዓት እንኳ ጌታን ታዞ ማድረግ በጣም ትልቅ ነገር ነው።

### 7. እንዴት ትንሽ ትእዛዝን የመታዘዝም ሆነ ያለ መታዘዝ ውጤት የትኛውም ዓይነት መሥዋዕትነት ከሚያካክሰው ይልቅ እጅግ ሊበልጥ ይችላል

ሔዋን እግዚአብሔርን ባለመታዘዟ ምክንያት የገባንበትን ውጥንቅጥ ተመልከት። እግዚአብሔር አምላክ በኤደን ገነት ውስጥ ሲጠይቃት



(ምንድር ነው ያደረግሽው?) ብሎ ነበር። ወደዚህ ዓለም ያመጣሽው ይህ ሁሉ ጦርነት ምንድር ነው? እነኚህ የፈጠርሻቸው ሕመሞች ምንድር ናቸው? ይህን ዓለም ያስተዋወቅሽው መዛባት ምንድር ነው? በሰው ዘር ላይ ያመጣሻቸው እነኚህ ካንሰሮችና ኤች አይ ቪ ምንድር ናቸው? እነኚህ የወለድሻቸው ሳዳም ሁሴን፣ አዶልፍ ሂትለር እና ስታሊን የሚባሉ ገጸ ባሕርያት ምንድር ናቸው? እነኚህ ያመጣሻቸው ቀብሮችና ሞቶች በሙሉ ምንድር ናቸው? በዚህ ዓለም ላይ ከፍተኛ ስፍራ የያዙ ፍርሃትና ራስህን አድን ምንድር ናቸው? እነኚህ አንቺ ያነሣሻቸው በሴቶች ላይ ያሉ መካንነት እና ሥቃይ ምንድር ናቸው? እነኚህ እንዲያስፈልጉን ያደርግሻቸው ሆስፒታሎች ምንድር ናቸው? እነኚህ ያፈራሻቸው አካለ ስንኩላን፣ ዓይነ ስውራን፣ እና ሽባ የሆኑ ሰዎች እነማን ናቸው?

ሄዋን በአንድ ያለመታዘዝ ተግባሯ የምታመጣውን አላወቀችም ነበር። ወደዚህ ዓለም የምታመጣውን ጉዳትና ሥቃይ መገመት አልቻለችም ነበር። ይህ ነው በአገልግሎት እንድቆይ የሚያደርገኝ አንዱ ሐሳብ። እግዚአብሔርን ባልታዘዝ ኖሮ ሊጠፋ የሚችለውን ሕዝብ አስባለሁ። ስለ ኢየሱስ አስብ። በአገልግሎቱ ስለ ዳኑ ሰዎች ሁሉ አስብ። በአንድ የመታዘዝ እርምጃ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩትን ከሲኦል አዳነ።

ምናልባት እስከ ስማንያ ዓመት በመቆየት፣ ከአገር ወደ አገር እየዞረ ቢሰብክ ኖሮ፣ ዛሬ ያገኘውን ፍሬ ባላፈራ ነበር።
በእግዚአብሔር ዓይን መታዘዝን የመሰለ ነገር የለም። መታዘዝ ከመሥዋዕትነት ይበልጣል።

> እንግዲህ **በአንድ በደል ምክንያት** ፍርድ ለኩነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደመጣ፣ እንዲሁም **በአንድ ጽድቅ ምክንያት** ስጦታው ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ።
>
> ሮሜ. 5፡18

ይህ ስለ መታዘዝ ልትማረው የሚገባው በጣም አስፈላጊ የሆነ እውነት ነው፡፡

መድፉን በሆነ ዒላማ ላይ እንዲተኩስ ትእዛዝ የደረሰው የመቶ አለቃ ታሪክ ትዝ ይለኛል፣ ዒላማውም የሚገኘው በተወሰነ ማይል ርቀት ላይ ነበር፡፡ ለመተኮስ ሲዘጋጁ፣ የሬዲዮ መገናኛው ሠራተኛ የመቶ አለቃው ተኩሱን እንዲያዘገይ የሚያደርግ አዲስ ትእዛዝ ይዞ እየሮጠ መጣ፡፡ ቀድሞ በጠላት ተይዞ የነበረው ስፍራ፣ በራሳቸው ሠራዊት ተያዘ፡፡ ይሁን እንጂ የመቶ አለቃው ለመዋጋት ካለው ከፍተኛ ቅናትና ጉጉት የተነሣ የሬድዮ ኦፕሬተሩን አልሰማውም፡፡ ወደ ጦርነቱ ውስጥ ለመግባት በጣም ተመስጦ ስለነበር አላደመጠም፡፡ በታሪኩ ውስጥ፣ የሬድዮ ኦፕሬተሩ የመቶ አለቃው አዲሱን ትእዛዝ እንዲሰማ ሲማጠነው በጥይት እንደተመታ ይናገራል፡፡ ግን ዋጋ አልነበረውም፡፡ መልእክቱን ከማስተላለፉ በፊት ሞተ፡፡ የመቶ አለቃው በመጨረሻ ጠላት ነው ብሎ ባሰበው ይዞታ ተኩስ በመክፈት ድብደባ አካሄደ፡፡

ወዲያው፣ ባደረገው ድብደባ ምክንያት የገዛ ወታደሮቹን እንዳጠቃ እና ብዙዎች እንደቆሰሉ ወሬ ደረሰው፡፡ የራሱ የሆኑትን እንዳጠቃና እንደገደለ ተነገረው፡፡ ይህ ሰው በኋላ የጦር ፍርድ ቤት ቀረበ፡፡

ከዚህ ታሪክ፣ መታዘዝ እንዴት ከመሥዋዕትነት እንደሚበልጥ እናያለን፡፡ ወጣቱ የመቶ አለቃ የፈለገው ይምጣ ብሎ መዋጋት ፈለገ፡፡ ግን በዚያ ሰዓት ማድረግ የሚገባው ትልቁ ነገር መተኮሱን መተው ነበር፡፡ ተኩሳችንን ማቆም የሚገባን ጊዜ ይኖር ይሆን?

እግዚአብሔር ልክ ሁሉንም ገጽታ እንደሚመለከት ጄኔራል ነው፡፡ መቼ መሥዋዕትነት እንደሚያስፈልግ እና እንደማያስፈልግ ያውቃል፣ መቼ መተኮስ እንደሚያስፈልግና እንደማያስፈልግ ያውቃል፡፡ መታዘዝ ከመሥዋዕትነት እንደሚሻል ተማርሁ፡፡



እግዚአብሔር በልማድ የምናደርጋቸውን ነገሮች እንዳናደርግ ጠይቆናል፡፡ እግዚአብሔር ስላለን ከመስበክ ይልቅ አለ መስበክ የሚበልጥበት ጊዜ ይኖር ይሆን? ሐዋርያው ጳውሎስ የተለያዩ ትእዛዞችን በጌታ እንደታዘዘ ይናገራል፡፡ በአንድ ወቅት፣ እንዲጠግብ ሲታዘዝ በሌላ ጊዜ ደግሞ እንዲራብ ታዟል፡፡ ጳውሎስ ትኩረቱ ጌታን በመታዘዝ ላይ ነበር፡፡ ትእዛዙ ረሃብ ከሆነ፣ ለዚያ ዝግጁ ነበር፤ ትእዛዙ መጥገብ ከሆነ፣ ይታዘዝ ነበር!

> መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ፤ በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ **መጥገብንና መራብንም መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ፡፡**
>
> ፊልጵስዩስ 4፥12

## የሳኦል አለመታዘዝ

ሳኦል ከእግዚአብሔር ይልቅ እርሱ ጥበበኛ እንደሆነ በማሰብና አለመታዘዙን በማካካስ ሲገለጽ የሚችል ዓይነተኛ ምሳሌ ነው፡፡ የትኛውም መሥዋዕት፣ የፈለገውን ያህል ትልቅ ቢሆን እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ የተደረገ ከሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡ እግዚአብሔር ደስ ያልተሰኘባቸው ብዙ መሥዋዕቶች አሉ፡፡ እግዚአብሔር መሥዋዕትነትን አይቃወምም፣ ግን መጀመሪያ መታዘዝህን ይፈልጋል፡፡

> **የመሥዋዕታችሁ ብዛት ለእኔ ምን ይጠቅመኛል?** ይላል እግዚአብሔር የሚቃጠለውን የአውራ በግ መሥዋዕትንና የፍሪዳን ስብ ጠግቢያለሁ፤ የበሬና የበግ ጠቦት የአውራ ፍየልም ደም ደስ አያሰኘኝም፡፡
>
> ኢሳይያስ 1፥11

## የኢያሱ አለመታዘዝ

ኢያሱ በተስፋይቱ ምድር ላይ የሚገኙትን አሕዛብ ሁሉ የማጥፋት ግልጽ አደራ ተሰጥቶት ነበር፡፡ ይህን ትእዛዝ አለመታዘዝ እነኚሁ ሰዎች በእስራኤላዊያን ላይ ወጥመድ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሆነ ተገልጾለት ነበር፡፡

> የአገሪቱንም ሰዎች ከፊታችሁ ባታሳድዱ ያስቀራችኋቸው ለዓይናችሁ እንደ እሾህ ለጎናችሁም እንደሚወጋ ነገር ይሆኑባችኋል በምትቀመጡባትም ምድር ያስጨንቁአችኋል፡፡
>
> ዘኍልቁ 33፡55

ይሁን እንጂ፣ ኢያሱ ሦስት ቁልፍ በሆኑ ከተሞች ውስጥ አሕዛብን ተወ፡፡ እግዚአብሔርን ከጋዛ፣ ጌት እና አዛጦን በቀር በሁሉ ስፍራዎች ታዘዘ፡፡ ራስህ አንብበው፡፡

> ኢያሱም ብዙ ዘመን ከእነዚህ ነገሥታት ሁሉ ጋር ይዋጋ ነበር፡፡ በገባዖን ከሚኖሩ ከኤዊያውያን በቀር ከእስራኤል ልጆች ጋር እርቅ ያደረገች አንዲት ከተማ አልነበረችም፤ ሁሉን በሰልፍ ያዙ፡፡ እግዚብሔርም ሙሴን እንዳዘዘ፣ ያጠፉአቸው ዘንድ ሞገስንም እንዳያገኙ ፈጽመውም እንዲያጠፉአቸው፣ ከእስራኤል ጋር ይጋጠሙ ዘንድ ልባቸውን እንዲያደነድኑ ከእግዚብሔር ዘንድ ሆነ፡፡ በዚያን ጊዜም ኢያሱ መጣ፤ ከተራራማውም አገር ከኬብሮን ከዳቤርም ከአናብም ከእስራኤልም ተራራማ ሁሉ ከይሁዳም ተራራማ ሁሉ የዔናቅን ልጆች ገደለ፤ ኢያሱም ከከተሞቻቸው ጋር ፈጽሞ አጠፋቸው፡፡ በጋዛ በጌትም በአዛጦንም ጥቂቶች ቀሩ እንጂ በእስራኤል ልጆች ምድር ከዔናቅ ልጆች ማንም አልቀረም፡፡ እግዚአብሔርም ለሙሴ እንደ ነገረው ሁሉ ኢያሱ ምድሪቱን ሁሉ ያዘ፡፡ ኢያሱም ለእስራኤል እንደ ክፍላቸውና እንደ ነገዳቸው ርስት አድርጎ ምድሪቱን ሰጣቸው፤ ምድሪቱም ከሰልፍ ዐረፈች፡፡
>
> ኢያሱ 11፡18-23

በጣም የሚደንቀው ኢያሱ በሕይወት የተዋቸውን ሦስቱን ቡድኖች ስትመለከት ነው፡፡ ጋዛ፣ ጌት እና አዛጦን፡፡ እነኚህ ሦስት ሕዝቦች እያንዳንዳቸው በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ዋነኛ ጠላቶች የሆኑ ሕዝቦችን ወለዱ፡፡ እግዚአብሔር አስቀድሞ ስላየ ነበር ያንን ትእዛዝ የሰጠው፡፡

እነኚህ ከተሞች የወደፊት የጠላቶች መፈልፈያ ሆኑ፡፡ የጌት ከተማ ጎልያድን አፈራች፡፡ በሳምሶን ሥጋ ውስጥ እሾህ የነበረችው ደሊላ ከጋዛ ነበረች፡፡ ዳጎን የተባለው ጣኦት፣ ባለበት መቅደስ ውስጥ የቃልኪዳኑ



ታቦት የተወሰደው፣ በአዛጦን ምድር ነበር፡፡ እነኚህ ጠላቶች የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደተዋጉ የኖሩ መሆናቸውን ስለነዚህ ሦስት የክፉ መልእክተኞች ማንም ረስቶ አያውቅም፡፡ ምናልባት፣ ባለመታዘዝህ ምክንያት፣ የእግዚአብሔርን የወደፊት ጠላቶች ትወልድ ይሆናል፡፡ መሥዋዕት የወደፊት ጠላቶች መምጣትን አይከላከልም፡፡ መታዘዝ ግን ይከለክላል፡፡

## የጌት ሰው የሆነው ጐልያድ

> ከፍልስጥኤማውያንም ሰፈር የጌት ሰው ጎልያድ ቁመቱም ስድስት ክንድ ከስንዝር የሆነ ዋነኛ ጀግና መጣ፡፡
>
> ፩ኛ ሳሙኤል 17፡4

## የጋዛዋ ደሊላ

> ሳምሶንም ወደ ጋዛ ሄደ . . . ከዚያም በኋላ በሶሬቅ ሸለቆ የነበረች ደሊላ የተባለች አንዲት ሴትን ወደደ፡፡
>
> መሳፍንት 16፡1,4

## የአዛጦኑ ዳጐን

> ፍልስጥኤማውያንም የእግዚብሔርን ታቦት ወስዱ ከአቤንኤዘርም ወደ አዛጦን ይዘውት መጡ፡፡ ፍልስጥኤማውያንም የእግዚአብሔርን ታቦት ወስደው ወደ ዳጎን ቤት አገቡት፤ በዳጎንም አጠገብ አኖሩት፡፡ በነጋም የአዛጦን ሰዎች ማለዱ እነሆም ዳጎን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በምድር ላይ በግንባሩ ወድቆ ነበር ዳጐንንም አንስተው ወደስፍራው መለሱት፡፡
>
> ፩ኛ ሳሙኤል 5፡1-3

እግዚአብሔር በእኛ ዘመን ካሉት የጌት፣ ጋዛ እና አዛጦን ከተሞች ያድነን!

***ከዚህም ሁሉ በላይ፤ ልጄ ሆይ፤ ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም!***

ከብዙ ዓመታት በፊት በዓለም ውስጥ ሁለት ዓይነት ሰዎች እንዳሉ ተማርሁ። ታንኳውን ከአሸዋው እስከ ባሕሩ ድረስ የሚገፉ አሉ። ከዚያም ታንኳው በውሃ ላይ በሰላም ሲንሳፈፍ ዘለው የሚወጡ አሉ።

ታንኳው በአሸዋ ላይ ሲሆን፣ ወደ ውሃው እስኪገባ መግፋት በጣም አስቸጋሪ ነው። ውሃ ላይ ከሆነ በኋላ ግን ደኅንነቱ የተጠበቀ ስለሆነ ብዙ ሰዎች ዘለው ይገቡበታል። ለዚያ ነው ለትልቅ ቤተ ክርስቲያን ማደግ ቀላል የሚሆነው።

አገልግሎት ስጀምር ተንቄና ተቋውሞ ገጥሞች ነበር! ዞር ብዬ ሳየው፣ ቤተ ክርስቲያን ስጀምር የነበረውን ወጀብ ማለፍ መቻሌ ይደንቀኛል። አንዳንዴ፣ በቃኝ ለማለት የምፈልግባቸው ጊዜዎች ነበሩ። በዓለም ላይ ያለ ሰው ሁሉ የተነሣብኝ ይመስል ነበር። ብዙ ስም አወጡልኝና ተሳለቁብኝ።

ከሕክምና ትምህርት ቤቴ ሆስቴል ወደ መማሪያ ክፍል ታምቡር ተሸክሜ ስሄድ፣ በቅንአት የተሞላ እብድ ሳልመስል አልቀርም! "ይህ ሰው ጥቂት የሕክምና እና የነርሲንግ ተማሪዎችን ይዞ ምን መሥራት የያዘ ይመስለዋል?"

በእኔ ዘመን ከነበሩ ትላልቅ ቤተ ክርስቲያኖች አንዳችም እገዛ አላገኘም ነበር። አንዳንዶቹ ሲሳለቁብኝ ሌሎቹ ደግሞ ጭራሽ ይቃወሙኝ ነበር። ከማንኛውም የእግዚአብሔር ሰው ድጋፍ ወይም ማረጋገጫ አላገኘም ነበረ።

## አትጨናነቅ

በአገልግሎትህ ጅማሬ ላይ ለገንዘብ አትጓጓ። ለኑሮ የሚያስፈልግህን ገንዘብ ለማግኘት በጀመርከት ቤተ ክርስቲያን ላይ አትደገፍ። ያ ትልቅ ስሕተት ነው! ያንን ካደረግህ፣ ለመኖር ስትል ነፋስ ለመጨበጥ ትሞክራለህ።



አብዛኛውን ጊዜ ትንሽ ቤተ ክርስቲያን የመጋቢውን ደመወዝ መክፈል አትችልም፣ መኪና መግዛት ደግሞ ይባስ። **ቤተ ክርስቲያን ስሚጀምር ማንኛውም ሰው የምመክረው ሥራ ማግኘትና ቤተ ክርስቲያኑ የትርፍ ጊዜ አገልጋይ ሆኖ መጀመርን ነው።** ሰዎች የምታገለግለው ለገንዘብ ስትል እንዳልሆነ ሲመለከቱ፣ በአዲሷ ቤተ ክርስቲያንህ ይበልጥ ይሳባሉ።

ብዙ መጋቢዎች ከጥቂት አባሎቻቸው ብዙ መባ ለማግኘት ይጨነቃሉ። ዐሥራ ስድስት ሰዎች አንተን መንከባከብ አይችሉም። ሃያ አንድ ሰዎች ሊደግፉህና የልጆችህን ትምህርት ቤት ወጪ ሊሸፍኑ አይችሉም። ተጨናቂ መጋቢ አትሁን! አሁኑኑ ሥራ አግኝ! በጊዜው፣ ቤተ ክርስቲያን መጋቢዎቿን የምትንከባከብበት ከበቂ በላይ የሆነ ገንዘብ ይኖራታል። ቤተ ክርስቲያንን ለመቋቋም ብዙ የራሴ ገንዘብ ማውጣት ጠይቆኛል። ምንም እንኳ አሁን በሙሉ ጊዜ አገልግሎት ውስጥ ብሆንም፣ ቤተ ክርስቲያን በተቋቋመችባቸው የመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት አይከፈለኝም ነበር።

በቤተ ክርስቲያን ጅማሬ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ደሞዝ ልትቀበል የማይገባበት ሌላም ምክንያት አለ። መሣሪያዎችን ለመግዛትና እንደ ቤት ኪራይ የመሳሰሉትን ወጪዎች ለመክፈል ገንዘብ ያስፈልጋል። የቤተ ክርስቲያኗ ደም ሥር የሆነው ገንዘብ ብትመጥ፣ ትክክለኛ እድገት ሊኖራት አይችልም።

## ሁለት ወይም ሦስት ይበቃል

ቤተ ክርስቲያን ለመጀመር ምን ያህል ሰዎች ያስፈልጋሉ? መልሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ! ሁለት ወይም ሦስት!

**ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ።**
**ማቴዎስ 18:20**

በቤተ ክርስቲያኔ ውስጥ ያሉኝ ሰዎች ሁለትና ሦስት ስለሆኑ የተቹኝ ሰዎች አሉ። ይሁን፣ እንዲህ ዓይነቱ ትችት የሚመጣው ከአላዋቂዎች ነው። እንዲህ ዓይነት ትችቶችንና ልምድ የጎደላቸው አሉባልታዎች ከመስማት የውሻዬን የማለዳ ጩኸት መስማት እመርጣለሁ!

እኔ ቤተ ክርስቲያኔን የጀመርሁት የሌላውን ሰው ቤተ ክርስቲያን ግማሽ በመገንጠል አይደለም። እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ዝግጁ የሆነ አንድ መጋቢ ካለኝ፣ ማድረግ የሚገባኝ እርሱን ልኮ ሥራውን እንዲጀምር ማድረግ ብቻ ነው። ሳይትሃውስ ካቴድራል የተጀመረችው አምስት በሚያህሉ ሰዎች ነው።

ቤተ ክርስቲያን ለመጀመር ወደ ዙሪክ ስሄድ፣ የማውቀው አንድ ሰው ብቻ ነበር። ዛሬ ያች ቤተ ክርስቲያን በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች አሉባት። በደቡብ አፍሪካ ውስጥ አንድም ሰው የማያውቅ አንድ መጋቢ፣ ግን የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ፈቃደኛ ሆነ፣ በደቡብ አፍሪካ የምትገኘውን ቤተ ክርስቲያናችንን ጀመረ። ቤተ ክርስቲያን ለመጀመር ከአንድ ሰው በላይ አያስፈልግህም። ሦስት ሰው ብቻ ያለባቸው ቤተ ክርስቲያናት አሉኝ፣ ይህን ማለት አያሳፍረኝም። የማንንም ትኩረት ለመሳብ አትሞክር፣ ብቻ የእግዚአብሔርን ሥራ ሥራ!

አንዳንድ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ለመጀመር የሚፈሩት መሠረታዊ የሆኑ የክርስቲያን ሥራዎች መሥራት ስለማይችሉ ነው። መሠረታዊ ነገሮች ስል ምን ማለቴ ነው? መሠረታዊ ነገሮች ጸሎት፣ መመስከር እና የተለወጡ ሰዎችን መከታተል ነው።

በእውነት በእግዚአብሔር ከተጠራህ የሚያስፈልገው ብቸኛ ሰው አንተው ራስህ ነህ! በዚህ መንገድ የጀመሩ ቤተ ክርስቲያናት ሁሉ ትልቅ ዛፎች ሆነዋል። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መንግሥት የሰናፍጭ ቅንጣት እንደምትመስል ይናገራል።



... መንግሥተ ሰማያት ሰው ወስዶ በእርሻው የዘራትን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላለች እርስዋም ከዘር ሁሉ ታንሳለች፣ አደገችም ጊዜ ግን፣ ከአታክልቶች ትበልጣለች የሰማይም ወፎች መጥተው በቅርንጫፎችዋ እስኪ ሰፍሩ ድረስ ዛፍ ትሆናለች።

ማቴዎስ 13፡31,32

ያ ምን ማለት ነው? የእብሮ አደጎች ማኅበር ወይም የአካል ብቃት ክለብ በብዙ ሰዎች ሲጀምር፣ የቤተ ክርስቲያን አጀማመር እንደ መናኛ ዘሮች ነው። ግን ማደግ ይችላሉ። ብዙዎቹ መጋቢዎቹ ቤተ ክርስቲያኖቻቸው ሲያድጉ ይደነቃሉ። ቤተ ክርስቲያኗ እንደምታድግ አያምኑም። አጀማመሩ በጣም ደሳሳ ይመስላል፣ ግን የእግዚአብሔር መንግሥት አጀማመሩ እንዲያ ነው።

## አንድ አባል የነበራት ሜጋ ቤተ ክርስቲያን!

አንድ ቀን፣ ከመጋቢዎቼ አንዱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄድ አንድ ሰው ብቻ መጣ። ተስፋ እንደቆረጠ እና እንደተጨነቀ ነገረኝ። ያንን አንድ ሰው በአምልኮ መራ። ከዚያም ለእዚያ አንድ ሰው ሰበከ። ቀጥሎም ከዚያ አንድ ሰው መባ ሰበሰበ እና አገልግሎቱን ፈጸመ። እንዴት በሕይወቱ የመጨረሻ በሆነ ጥልቅና በጨለመ ተስፋ መቁረጥ ወደ አፓርትመንቱ እንደተመለሰ ተረከልኝ። ዛሬ ቤተ ክርስቲያኑ ሜጋ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነችና አሁንም በማደግ ላይ መሆኗን ስነግራችሁ በጣም ደስተኛ ነኝ።

## አትቸኩል

በአንድ ሌሊት ከዘር ወደ ትልቅ ዛፍነት የተቀየረ ዛፍ የለም። የትኛውም የሰው ልጅ በአንድ ዓመት ስድስት ጫማ ርዝመት ሊያድግ አይችልም። የትኛውም የሁለት ዓመት ልጅ በስድስት ወር ውስጥ የአሥራ ስምንት ዓመት ሰው ወደ መሆን አያድግም። ችኩል መንፈስ ካለህ፣ ቤተ ክርስቲያን በመጀመር ስኬታማ መሆን አትችልም።

ስስታም፣ ሀብት ለማከማቸት ይስገበገባል፤ ድኽነት እንደሚጠብቀው አያውቅም።
ምሳሌ 28:22
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

በእርግጥ፣ ስትቸኩል፣ አቋራጭ መፈለግህ አይቀርም፣ የሌላውን ቤተ ክርስቲያን ታፈርሳለህ፣ ከአንተ የሚበልጡትን ትተቻለህ። በአገልግሎትህ ስጋ ዕድሜ ላይ አደገኛ ኃጢአቶችን ትፈጽማለህ። በአንድ ዓመት ውስጥ ብዙ አትጠብቅ። ከሁለት ዓመት በኂላ ሃያ ሰው ቢኖርህ አትደነቅ። በእርግጥ የሰናፍጭ ቅንጣት ትልቅ(ሜጋ) ቤተ ክርስቲያን ሆና ታድጋለች!

## ምሶሶዎች እንዲሰጡህ ጸልይና መልምል

ስለ ሠራተኞች ጸልይ፣ እግዚአብሔር ረዳቶች እንዲሰጥህ ጸልይ። ከዚያም ወጥተህ ቤተ ክርስቲያን ምሶሶ የሚሆኑ ሰዎችን መልምል። ኢየሱስ ሰዎች እንዲከተሉት ጠርቷል። ኢየሱስ ስምዖንን እና እንድርያስን መለመለ። በተጨማሪም ያዕቆብንና ዮሐንስን መለመለ።

በገሊላ ባሕርም አጠገብ ሲያልፍ ስምዖንን ወንድሙንም እንድርያስን...አየ። ኢየሱስም፡- በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ አላቸው።
ማርቆስ 1:16,17

ከዚያም ጥቂት እልፍ ብሎ የዘብዴዎስን ልጅ ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን... አየ። ወዲያውም ጠራቸው አባታቸውንም...ትተው ተከትለውት ሄዱ።
ማርቆስ 1:19,20

እነ'ኚህ ሰዎች በኋላ የቤተ ክርስቲያን አዕማድ ሆኑ።

እንደ አዕማድ የሚቆጠሩት ያዕቆብ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስም...
ገላቲያ 2:9
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)



አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ አስፈላጊ የሆኑ የቤተ ክርስቲያን አዕማዶች ወደ ቤተ ክርስቲያንህ እንዲቀላቀሉ ለማሳመን ሩቅ መጓዝ ይጠይቃል። የራስህን ቤተ ክርስቲያን በምትገነባበት ጊዜ የሌላውን ሰው ቤተ ክርስቲያን እንዳታፈርስ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባሃል።

ለሁሉም ግልጽ ጥሪ ማድረግ ሰዎች ወደ አንተ እንዲመጡ ከማስገደድ ይለያል። የቤተ ክርስቲያን ሕልውና ያለው ግልጽ ጥሪ በማድረግ ላይ ነው። እስታውስ የዘራኸውን ያንኑ ታጭዳለህ(ገላቲያ 6:7)። የሌላው ሰው ቤተ ክርስቲያን አዕማዶች ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲለቁ ግፊት ካሳደርክ አንድ ቀን በአንተም ላይ ይኸው ይሆናል።

ሰዎችን የመመልመል አንዱና አስፈላጊ መንገድ ሠራተኞች እንዲሰጡህ መጸለይ ነው። የዕለት ተዕለት ጸሎትህ ይሁን። እግዚአብሔር ሠራተኞችንና የተሰጡ ሰዎችን እንዲሰጥህ ጠይቀው። በምታደርገው ነገር ላይ ሁሉ ታማኝ የሚሆኑልህ ሰዎች እንድታገኝ ጸልይ። የሚደግፉህ ሰዎች እንድታገኝ ጸልይ።

ስለዚህ የመከሩ ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ ለምኑት።
ማቴዎስ 9:38
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

## የጸሎት መሠረት ጣል

እኔ ቢያንስ ቢያንስ የሦስት ሳምንት ወይም ከዚያ በላይ የጾም ጸሎት ጊዜ ቢኖር የሚል ሐሳብ አቀርባለሁ። ስለ ቤተ ክርስቲያኗ የወደፊት ሁኔታ ጸልይ። በሚቀጥለው ሳምንት ውጤት እያለሁ ብለህ አትጠብቅ። የእነኚህ ጸሎቶች ውጤት በፊትህ ባሉ ዓመታት ውስጥ የሚታዩ ናቸው።

ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኮሌ - ቡ (ቤተ ክርስቲያናችን ወደምትገኝበት የአክራ አካባቢ) ስመጣ፣ ከአራት የሕክምና ተማሪ ጓደኞቼ ጋር በየዕለቱ

ከምሽቱ አራት ሰዓት ላይ ወደ ባሕር ዳርቻ በመሄድ እጸልይ ነበር:: እስከ እኩለ ሌሊት እንጸልይ ነበር:: በባሕሩ ዳር የሚገኙ ዐለቶች ላይ ቆሜ፣ የምጸልየው ጸሎት ቀላል ነበር፣ "ጌታ ሆይ፣ ፈቃድህ ይፈጸም:: በሕይወቴ ልታደርግ የወደድከውን አድርግ::" ዓመታቱ ሲያልፉ፣ ጌታ እነዚህን ጸሎቶች ከምገምተው በላይ መለሰ::

በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ጅማሬ ላይ ጠንካራ የሆነ የጾምና ጸሎት መሠረት በመጣል አምናለሁ:: ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አካል እንጂ ማሕበራዊ ክበብ አይደለችም:: በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እና መንፈሳዊ መሠረቶች ላይ መመሥረት አለባት::

ለቤተ ክርስቲያን ምሥረታና እድገት ጸሎት ጠቃሚ ከሆኑ የጸሎት ጥቅሶች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው::

... ፈቃድህ ይፈፀም...

ማቴዎስ 6:10

... መንግሥትህ ትምጣ...

ማቴዎስ 6:10

... ለምነኝ አሕዛብን ለርስትህ ... እሰጥሀለሁ::

መዝሙር 2:8

... አገሬንም አስፋ...

፩ኛ ዜና 4:10

... ሰውንም እንደ መንጋ አበዛላቸዋለሁ::

ሕዝቅኤል 36:37

... ጽዮን እንዳማጠች ወዲያው ልጆችዋን ወልዳለችና::

ኢሳይያስ 66:8

... ስለ እናንተ ምጥ ይዘኛል::

ገላቲያ 4:19



## የምታበረታታ መሪ ሁን

ጥቂት ሰዎችን በክፍል ውስጥ ከሰበሰብህ በኋላ፣ በከፍተኛ ሁኔታ ልታበረታታቸው ይገባሃል፣ ራስህንም ጭምር:: ሰዎች በአዕምሮአቸው እንዲህ ብለው ያስባሉ፤ "እብደሃል እንዴ? ይህን ነው ቤተ ክርስቲያን ብለህ የምትጠራው?" ዳዊት ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር ሲገጥመው ያደረገውን ነገር ልትለምደው ያስፈልግሃል:: በመጀመሪያ ራስህን አበረታታ::

ዳዊት ግን በአምላኩ በእግዚብሔር ልቡን አበረታ::

፩ኛ ሳሙኤል 30:6

ከዚያም ሕዝቡን ማበረታታት አለብህ:: ጅማሬው ታናሽ ቢመስልም፣ የወደፊት ፍሬው ግን ታላቅ እንደሚሆን ንገራቸው!

ጅማሬህም ታናሽ ቢሆንም እንኳ ፍጻሜህ እጅግ ይበዛል::

ኢዮብ 8:7

ታናሽ ጅማሬን እንዳይንቁ ንገራቸው:: ሁልጊዜ ፍጻሜ ከጅማሬ ይተሻለ እንደሚሆን ንገራቸው:: እንደ ተበረታታህ ሲመለከቱ፣ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ጋር ለመዝለቅ ይበረታታሉ::

የነገር ፍጻሜ ከመጀመሪያው ይሻላል...

መክብብ 7:8

የጥቂቱን ነገር ቀን የናቀ ማን ነው?

ዘካርያስ 4:10

የታላቅ ቤተ ክርስቲያን መሥራች አባላት በመሆናቸው የታደሉ እንደሆኑ ንገራቸው:: የአንድ ሕንፃ ዋነኛው ክፍል መሠረቱ እንደሆነ ግለጽላቸው:: ስለዚህ፣ ቤተ ክርስቲያኗ ሊኖራት የሚችል በጣም አስፈላጊ አባላት እንደሆኑ ንገራቸው:: ኢየሱስ መሥራች አባላቶቹ

ለነበሩት ሐዋርያት ሁል ጊዜ ልዩ ስፍራ እንደነበረው እና ልዩ ሽልማት እንደነበረው ንገራቸው።

በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል...

ኤፌሶን 2:20

የመገሠጽን እና የመጮህ ስሕተትን አትፈጽምባቸው። በጥቂት አባላቶችህ ላይ ጭንቀትህን አትወጣ። በቤተ ክርስቲያኒቱ የጅማሬ ዕድሜ ላይ ትንሽ መሆኗ የእነርሱ ጥፋት አይደለም። እምነትን ስበክ! ተስፋን ስበክ! መረጋጋትን ስበክ! ስለተሻለ ነገ ስበክ! ሰዎች ነገ ከዛሬ እንደሚሻል መስማት ይወዳሉ። በስብከትህ ደፋር እና የማታፍር መሆን አለብህ።

እላችኋለሁ፣ ወዳጁ ስለሆነ ተነሥቶ ባይሰጠው እንኳ፣ ስለ ንዝንዛው ተነሥቶ የሚፈለገውን ሁሉ ይሰጠዋል።

ሉቃስ 11:8

ከላይ ባለው ንባብ ውስጥ፣ የግሪኩ ቃል "አናዲያ" ንዝነዛ ተብሎ ተተርጉሟል፣ ዕፍረተ ቢስ መሆን ማለትም ነው። ያለ ዕረፍት የሚጸና ሰው ውጤት ያገኛል። እንጋፈጠው! በጥቂት ሰዎች አገልግሎት መጀመር በተወሰነ ደረጃ ያሳፍራል። ለዚህ ነው ሰዎች ታናሽ ጅማሬን የሚንቁት። ዕፍረተ ቢስነት "አናዲያ" በቤተ ክርስቲያን ጅማሬ ላይ የምታደርገው ነገር ሁሉ መገለጫ መሆን አለበት። ያለ ዕፍረት ሰዎች እሁድ ማለዳ እንዲመጡ ጋብዝ። በቤተ ክርስቲያን እንደማታፍር ሲመለከቱ የመምጣት ፍላጎት ይኖራቸዋል። ቤተ ክርስቲያንን ያለ ዕፍረት አስተዋውቅ። ስለ ቤተ ክርስቲያን የምትናገረውን ያምናሉ። ረዳት ካለህ ስለ ስብከቱና በአጠቃላይ ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ መልካም ነገሮች መናገር አለበት። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ለቤተ ክርስቲያኒቱ እድገት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ።



## መመስከር እና መከታተል

ከቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴዎችህ ሁሉ ይህ ተቀዳሚ መሆን አለበት። በከተማው ወዳሉ ቤቶች በድፍረት በመግባት ለሰዎች ክርስቶስን መስበክ አለብህ። ሰዎችን በቤታቸው ውስጥ ያለ ዕፍረት ወደ ክርስቶስ መምራት አለብህ። ጸልይላቸውና ወደ ቤተ ክርስቲያን ጋብዛቸው።

በጎዳና ላይ ቆመህ ለሚያልፉ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ንገር። የጎዳና ላይ ወንጌል ስብከት ያለ ዕረፍት ማድረግ ካልቻልህ መጋቢ መሆን አትችልም። ጉባዔው እሁድ ሰዎችን እንዲጋብዝ ምራ። ብዙዎቹ ጎብኚዎች ተመልሰው ባለመምጣታቸው አትዘን። ብዙዎቹ በምንም ዓይነት አይጸኑም። እግዚአብሔር መለኮታዊ በሆነ መንገድ መብዛትን ያመጣል።

መጋቢዎች የመዝራት እና የማጨድ መንፈሳዊ መርህ እንዳለ ሊያውቁ ይገባል። የዘራኸውን ያንኑ ታጭዳለህ።

ሰው የዘራውን ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና . . .

ገላቲያ 6:7

በመጋበዝና በመመስከር ዘሮችን ብትዘራ፣ አንድ ቀን ከዚያው ታጭዳለህ። የእኔ ልምድ በመጀመሪያ አካባቢ ክሩሴድ ወይም የወንጌል ስርጭት ከወጣን በኋላ የምናገኘው ውጤት እጅግ አናሳ ነበር። ይሁን እንጂ፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የወንጌል ስርጭት ካካሄድንባቸው ቦታዎች ሰዎች ይመጡ ጀመር። አብዛኛውን ጊዜ የሚመጡት እኛ የመሰከርንላቸው ሰዎች አይደሉም፦ ግን እግዚአብሔር መለኮታዊ በሆነ መንገድ ከዚያ ቦታ ወደ እኛ ይልካቸዋል። የ 'አናካዞ' መርሆዎችን በሙሉ ተጠቀም (ለበለጠ ጥናት 'አናካዞ' የሚል ርዕስ ያለው የቢሾፕ ዳግ ሂዋርድ ሚልስ መጽሐፍ ተመልከት)

አባላቶችህን አስተምር፣ የእድገት ፍንዳታ ከፈለግህ፣ መሪዎችህን አስተምር!

መሪዎችን ማስተማር በሥርህ የሚሠሩ መሪዎች ላይ ሥልጣንህ እንዲመሠረት ያደርጋል። ይህ የሚሆንበት ምክንያት በመሪዎችህ ላይ ያለህ ሥልጣን የሚገለጸው እነርሱን የመመገብ ችሎታህ ነው። ተራ አባላትን ማስተማር በዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ላይ ሀብትን ማፍሰስ ነው። መሪዎችን ማስተማር ደግሞ አንተ ካለፍህ በኋላ በሚኖረው ትውልድ ላይ ሀብትን ማፍሰስ ነው። ተከታይ የሌለው ስኬት ውድቀት ነው!

እያንዳንዱ መጋቢ መሪዎችን ማስተማር አለበት ምክንያቱም ኢየሱስ ሁልጊዜ መሪዎችን ያስተምር ነበር። መጋቢ ተራ የቤተ ክርስቲያን አባላቶችን ከማስተማር ይልቅ ብዙ ጊዜውን መሪዎችን በማስተማር ማሳለፍ ይገባዋል። ይህ በኢየሱስ ክርስቶስ የተቀመጠልን ምሳሌ ነው። መሪዎችን ማስተማር የእውነተኛ መስፋት ታላቁ ቁልፍ ነው። መሪዎችን ካላሠለጠንህ ልትወክለው የምትችለው ማንም ሰው አይኖርህም።

እያንዳንዱ መጋቢ መሪዎቹን ማስተማር አለበት ምክንያቱም መሪዎች የሚሠሩትን ካላስተማርካቸው በስተቀር ምን ማድረግ እንደሚገባቸው አያውቁም። ብዙ መጋቢዎች በዙሪያቸው ያሉ ወደ ፊት መሪ መሆን የሚችሉ ሰዎች አስፈላጊውን እውቀት በስርጸት (Osmosis) የሚያገኙ ይመስላቸዋል። ሰዎች መሪነት በተፈጥሮ ለተሰጣቸው ልዩ ሰዎች ይመስላቸዋል። በስርጸት (Osmosis) የመሪነት ቁልፍ አይደለም ማስተማር እንጂ!

በዚህ ጉዳይ ላይ የጻፍኳቸው ብዙ መጽሐፍቶች አሉና እንድታነባቸው አሳስብሃለሁ፡- 'የትርፍ ጊዜ አገልጋዮች እና አገልግሎት'፣ ሜጋ ቤተ ክርስቲያን፣ የመጋቢነት አገልግሎትህን ወደ ላቀ ደረጃ ለውጥ፣ ወዘተ።



አባላቶችህን እነኚህን መጽሐፍት ስታስተምር፣ ምን እንደሚሆኑ ስታይ ትደነቃለህ።

## ቁልፍ 2 ስለ ታማኝነት ማስተማር

የቤተ ክርስቲያናትን መረብ የመዘርጋት ሁለተኛው ቁልፍ ታማኝነት ነው። ታማኝነት የቤተ ክርስቲያናት መረብ ለመዘርጋት መሠረታዊ ጉዳይ ነው። የምትተክላቸው ቤተ ክርስቲያናት በአንድ አካባቢ አይሆኑም። ስለዚህ ሰዎች ባሉበት አካባቢ ሁሉ ታማኞች ሊሆኑ ይገባቸዋል። በታማኝነት ላይ ብዙ አስተምሬአለሁ። 'ታማኝነት እና ታማኝ አለመሆን' እና 'መሪዎች እና ታማኝነት' በሚሉ ርዕሶች ሁለት መጽሐፍት ጽፌአለሁ። እነኚህን መጽሐፍት እንድታነብ እመክርሃለሁ፣ ለአገልግሎትህ መባረክ ይሆናሉ።

በአንድ ወቅት በታማኝነት ላይ በማስተማሬ የሆነ ሰው እንደተቸኝ ሰማሁ። እንዲህ አለ፣ "ለምን በታማኝነት እና ታማኝ አለመሆን ላይ ታስተምራለህ?"

በመቀጠልም ታማኝነት የምታስተምረው ነገር ሳይሆን ሰዎች በአመራርህ ተስበው የሚያደርጉት ነገር ነው አለ።

ይህ የእኔ ተቺ የቤተ ክርስቲያኑን እንዲት ቅርንጫፍ ሳይተክል ከአራት መቶ በላይ ቤተ ክርስቲያናትን የተከለ ሰውን ቢተች አይደንቀኝም።

በሌላ ጊዜ ደግሞ፣ አንድ ውድ መጋቢ በታማኝነት ላይ በማስተማሬ ተቸኝ። ይሁን እንጂ የእርሱ ቤተ ክርስቲያን ስትከፈል፣ የመጽሐፌ ትጉህ አንባቢ ከመሆንህ አልፎ መጽሐፌን ለሌሎች ሰዎች ማስተዋወቅ ጀመረ። ታማኝነት የታማኝነት ባል እስኪ መሠረት ድረስ ማስተማር የሚገባ ቁልፍ ርዕስ ነው!

## ቁልፍ 3. በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ላይ ማስተማር

ቤተ ክርስቲያን ማስተዳደር የተፈጠሩ ቤተ ክርስቲያናትን ማስተዳደር ያጠቃልላል። መንፈሳዊና ምድራዊ ጉዳዮችን አጣምሮ ማስተዳደር ተፈጥሮአዊ ነገሮችንና መለኮታዊ ነገሮችን ማመጣጠንን ይጠይቃል።

የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የተዋረድ እና ዲሞክራቲክ አስተዳደርን ማዋሃድ ይጠይቃል። እነኚህ ሁለቱም መንገዶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ምዕራፍ ስድስት ላይ ኮሚቴዎችን የማዋቀር ምሳሌን ያሳያል። የጳውሎስ እና የጢሞቴዎስ ሁኔታ ስናይ ደግሞ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የእዝ(ፈላጭ ቆራጭ) ቀጥተኛ ትእዛዝ የመስጠት አመራር ዘይቤ ምሳሌዎች እንዳሉት ያሳያል።

የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የእግዚአብሔርን ኃይል እና የእግዚአብሔርን ጥበብ ማቆራኘትን ይጠይቃል። **'የቤተ ክርስቲያን ሕስተዳደር'**፣ የሚለውን መጽሐፌን አንብብ።

ያለ መልካም የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የገነባኸው ሁሉ ቀስ በቀስ ይወድቃል። የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጠንቅቀህ ልታውቅ ይገባሃል አለበለዚያ አገልግሎትህ ከተተኮሰ ጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ወድቆ እንደ ተከሰከሰ ሮኬት ይመስላል።

> እግዚአብሔር ለጠራቸው ግን፣ አይሁድም ሆኑ ግሪኮች፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኃይል፣ የእግዚአብሔር ጥበብ ነው።
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 1:24
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)



## የቤተ ክርስቲያናት መረብ ጥቅሞች

1. በታሪክ እንደ ተረጋገጠው የቤተ ክርስቲያናት ወይም የአጥቢያዎች መረብ በጣም ስኬታማ ነው። እነኚህ የቤተ ክርስቲያናት መረብ አንዳንድ ጊዜ ዲኖሚኔሽንስ ይባላሉ።

2. ዛሬ በዓለም ላይ ብዙ በጣም የታወቁ የቤተ ክርስቲያናት መረቦች አሉ። እነኚህ መረቦች አብዛኛውን ጊዜ በሁሉም ስፍራ የረጉ እና በደንብ የተቋቋሙ ናቸው። ጉባዔ እግዚአብሔር (አሰምብሊስ ኦፍ ጎድ) ቤተ ክርስቲያን፣ ጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን፣ ቸርች ኦፍ ጎድ ኢን ክራይስት ታዋቂ ከሆኑት መረቦች ጥቂት ምሳሌዎች ናቸው። በዓለም ላይ ትልቅ የሆነችውና በዴቪድ ዮንግ ቾ መጋቢነት ሥር ያለችው ቤተ ክርስቲያን በአሰንብሊስ ኦፍ ጎድ ቤተ ክርስቲያን መረብ ሥር ትገኛለች።

3. ታሪክ እንደሚያሳየን የቤተ ክርስቲያናት መረብ አካል መሆን ትልቅ እና የተረጋጋ ጉባዔ እንዲኖር ያደርጋል። ምናልባት ለጉባዔህ የቤተ ክርስቲያን እድገት ቁልፍ ሊሆን ይችላል።

4. የቤተ ክርስቲያናት መረብ አካል መሆን ምናልባት ራስ ገዝ በሆኑ ጀማሪ ቤተ ክርስቲያናት ላይ የሚታየውን አለመረጋጋት ሊያስወግድ ይችላል። አንዳንድ ጊዜ በቤተ ክርስቲያናት መረብ ካለው ጥቅም አኳያ ሲታይ ጉዳቱ የጎላ አይደለም።

5. በቤተ ክርስቲያኖች መረብ ውስጥ፣ ወደ እናት ቤተ ክርስቲያናት የሚተሳሰሩ የተሞከሩና የተፈተኑ መርሆዎች አሉ።

6. በቤተ ክርስቲያናት መረብ ውስጥ፣ ታዋቂ የሆነው የቤተ ክርስቲያን ስም ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያኗ ይስባል። ይህ ስም እንደ ባለቤትነት መብት(franchise) በማገልገል ትልቅ ኃይል በመሆን ያገለግላል። የቤተ ክርስቲያናት መረብ ጥሩ ስም በቁጥር ሊገለጽ የማይችል ትልቅ መንፈሳዊ ጉልህነት አለው።

7. በቤተ ክርስቲያናት መረብ ውስጥ፣ የሠለጠኑ አባላት የተጠናከረ እና ክብር የሚሰጠው መጋቢነት ድጋፍ እና የሹመት አሠራር ተጠቃሚ ይሆናሉ።

8. የቤተ ክርስቲያናት መረብ አንዱ ለአንዱ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ተጠቃሚ ይሆናሉ። ከመረቡ ውጭ ካሉ አካላት የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት ላያስፈልግህ ይችላል። በወንድማማችነት የመደጋገፍ አሠራር ውስጥ፣ ቤተ ክርስቲያናት ብዙ መሥራት ይችላል።

9. የአንድ መረብ አካል የሆኑ የቤተ ክርስቲያን አባላት በቀላሉ ሊቀራረቡ ይችላሉ። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያናት መረብ በውስጡ ያሉ አባላትን በአንድነት ያቅፋል።

10. በአንድ መረብ ውስጥ ያሉ ቤተ ክርስቲያናት የመረቡ አካል ከሆኑ ትላልቅ አገልጋዮች በቀላሉ ተጠቃሚ ይሆናሉ። ፕሮቶኮል ጠብቀው ለመሄድ ወይም እነኚህን አገልጋዮች ለመጋበዝ የሚያስፈልገውን ወጪ ማውጣት አያስፈልጋቸውም።

11. በመረብ ሥር ያሉ መጋቢዎች ከታላላቆቹ አገልጋዮች አባታዊ ምክር እና ማበረታቻ መቀበል ይችላሉ። ራስ ገዝ የሆኑ ቤተ ክርስቲያናት መጋቢዎች ብዙውን ጊዜ አባት ነን ብለው የሚሰሉ አገልጋዮችን በጥርጣሬ እና በጥንቃቄ ይመለከታሉ። ራሳቸውን ችለው የሚንቀሳቀሱ ቤተ ክርስቲያናት ብዙውን ጊዜ



እርስ በርሳቸው ስለሚፎካከሩ እርስ በርሳቸው ከመደጋገፍ ይልቅ ያላቸው መተማመን ዝቅተኛ ነው።

12. ከአንድ መረብ ሥር ያሉ ቤተ ክርስቲያናት በአንድ መንፈሳዊ ከለላ ሥር ይሠራሉ። እንደ እውነቱም አንድ ቤተ ክርስቲያን ስለሆኑ አንድ ዓይነት ቅባት ይፈሳል።

*ከዚህም ሁሉ በላይ፣ ልጄ ሆይ፣ ተግሣጽን ስማ ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ፍጻሜ የለውም!*

## በዳግ ሂዋርድ-ሚልስ የተጻፉ ሌሎች ተወዳጅነትን ያተረፉ መጽሐፍቶች

*ታማኝነት እና ታማኝ አለመሆን

*መሪዎችና ታማኝነት

*የመጋቢነት አገልግሎትህን ወደ ላቀ ደረጃ አሳድግ

የአመራር ጥበብ

ሞዴል ጋብቻ

በድንቆችና በታአምራቶች ማገልገል

ሜጋ ቤተ ክርስቲያን

* የትርፍ ጊዜ አገልጋይ እና አገልግሎት

* ይህ ምልክት የተደረገባቸውን መጽሐፍቶች በአማርኛ፣ በስፓንሽ እና በፈረንሳይኛ ይገኛሉ። ከላይ የተገለጹትን ትርጉም መጽሐፍት በተመለከተ መረጃ ከፈለጉ በአድራሻችን ይጻፉልን።

## ስለ ጸሐፊው

ዳግ ሂዋርድ ሚልስ በአንዲት ጋና ውስጥ በምትገኝ የገጠር ከተማ የሕክምና ትምህርቱን በመከታተል ላይ ሳለ፣ አንድ ምሽት እግዚአብሔርን በጸሎት ሲጠባበቅ፣ ተዓምራዊ በሆነ ሁኔታ ቀባው። ልዕለ ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ "ካሁን ጀምሮ ማስተማር ትችላለህ . . ." የሚል ድምጽ በመስማት ተቀባ። ይህ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ጥሪ ነው ወደ ዓለም አቀፋዊ አገልግሎቱ ያመራው።

ዛሬ፣ "ፈዋሹ ኢየሱስ ክሩሴድ (HEALING JESUS CRUSADE) " የተሰኘው አገልግሎታቸው በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎችን የሚገኙበት እና በብዙ ተዓምራቶች የታጀበ ነው። እነዚህ አስደናቂ ተዓምራቶች በሕክምና ዶክተሮች የተረጋገጡ ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ ማየት የተሳናቸው ዓይኖች በርተዋል፣ መስማት የተሳናቸው ጆሮዎች ተከፍተዋል፣ ዊልቼሮች ባዶ ሆነዋል እንዲሁም ሙታን እንኳ ተነስተዋል።

ዳግ ሂዋርድ ሚልስ፣ በርካታ ተፈላጊ መጽሐፍ የጻፉና ዓለምአቀፋዊ ዲኖምኔሽን በመሆን ላይ የምትገኘው "የላይትሃውስ ቻፕል ኢንተርናሽናል" ቤተ ክርስቲያን መስራች ናቸው። የሬድዮ፣ ቴሌቪዥን እና የኢንተርኔት መርሃግብራቸው በመላው ዓለም በሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን በመድረስ ላይ ይገኛል። ሌሎች የወንጌል ስርጭት አገልግሎታቸው የመጋቢዎች እና የአገልጋዮች ኮንፍረንሶችን ማካሄድ እና እናካዘ የመጽሐፍ ቅዱስ አገልግሎት እና ስልጠና ማዕከልን ያጠቃልላል።